ምዕራፍ ሰባት

“ ቂጢኛም ከውርዴ ነው” አለቻት ቁስሏን ገላልጣ እያየች ሀሳብ ዋንም በሚገባ የተከታተለቻትና ያደመጠ ችላት የተረዳችላት መሆኗን ለመግለጽ ። ቀኑ የወር መግ ቢያ የልደታ ቀን ስለነበረ ሣር በተን አድርጋ ቆሎ አቅርባ ጪሳጪሱን አውዳ ሲስተር ፋናዬ ከሥራ እንደገባች ቡና የምታፈላው ምንተስኖት ነበረች ። የዘር ሆኖ ምንተስኖ ትም እንደ እናቷ ቡና ያምርላታል ።

ከቡናው ፊት ለፊት አካሏን አዝናንታ የተቀመጠ ችው ሲስተር ፋናዬ የምንተስኖትን የተከማቸ የሕይወት ገመና ሲጋራዋን እያጨሰች በአንክሮ ታዳምጣት ነበር ። ምንቴም ብሶትዋን ለምትረዳላት ለሲስተር ስታወጋ ስሜቷ ተሰምቷት የተሰበረ መንፈሷን ህልውናዋን ግል ጥልጥ አድርጋ ያየችላት መሆኑን ስለምታውቅ ከፍላ የስ ቀረችው ምስጢር አልነበራትም ። ምስጢር ሲከፋፈሉ ያለፉትን ሕይወት እየተረኩ ሲመለሱበት ይህ የመጀ መሪያው ባይሆንም ፤ ይነጋገሩበት የነበረው ከሳምንት በፊት በኮሚቴ ምርጫና ስብሰባ ሳቢያ ባልታለመና ባል ተጠበቀ አጋጣሚ ከውብሸት እንዳይላሉ ጋር ተገናኝ ተው በተፈጠረው ሁኔታ ሆስፒታል ከገባ በኋላ የሚገኝ በትን ደረጃ ሳትነግራት የጀመረችው ወግ ነበር ።

የተሰለበ ጠንካራ መንፈስዋን ፤ የተወጋ ህሊናዋን የተሰበረ ህልውናዋን አስታውሳ ደም አፍሳ ደም ለመ መለስ ስታልመው የኖረችውን የቀን ተሌት ሕልሟን ጊዜና ሁኔታ የራሳቸውን ፍርድና ውሳኔ ሰጥተው እጅ ዋን ሳትሰነዝር ጠላቴ ብላ በመንፈስ ታጥቃ ስትከታተ ለው የኖረችውን ውብሸት እንዳይላሉን ወድቆ ስላየችው የሚያመረቃ እርካታ እንዳልሆናት እየቆጫት ተናገረ ችው ። የዚህ እለት ንግግርዋ እንደዘወትሩ በእንባ አል ታጀበም ። ይልቁንም ቁጭት አግሏት አካልዋ ፈርጠም ዐይኖቿ ፈጠጥ አነጋገሯ ቆፍጠን ብሎ ነበር ። የልቧ ቋሳ በወጉ አልሻረላትም ነበርና ።

“ እኔም እንዳቸው የገደለኝን የመግደል ዓላማ ነበ ረኝ ።” አላቻት ሲስተር ሌላ ሲጋራ እያቀጣጠለች ። “ ገድሎ የመሞትን ዓላማ መመሪያዬ በማድረግ ራሴ በም መራውና በመሰለኝ በማቅደው ሕይወቴ ውስጥ እየኖ ርኩ ነው ። ሰውና የሰዎች ስብስብ በፈጠረውና በሚፈጥረው የማኅበራዊ ኑሮ ወግና ሥርዓት ከመጐተት ራሴን ነጻ አው ጥቻለሁ ። በኔና በኑሮዬ ላይ በርካታ ስሞች ይለጠፋሉ። ቢሆንም ደንታ የለኝም ፤ አይሰጠኝምም ። ከኅብረተሰቡም የአኗኗር ፈሊጥና ሕግ የሚያምረኝ የሚጥመኝ የለምና አልተቀላቀልኩም ። አልቀላውጠውምም ። ሰውና ሰዋዊ ገመናን እንድሸሸው የደረገኝ ሰው ለራሱ ሲል በፈጠረው የግንኙነት ሥርዓት አንዱ ሌላውን ጐን እየጐዳው ማየቴ ነው ። በህሊና ሚዛን ድርጊቱን የማጤነውና የምነቅፈው በመጻረርና በመጥላት ነው ። ምክንያቱም ይህ ሁኔታ ለኔም እስከ መቃብር የሚደማ ቁስል ተክሎ ብኛል ” አለቻት ሲስተር ከተቀመጠችበት ተነስታ በዚያችው እፍኝ በምታህል ቤት ውስጥ እየተንጐራደደች በመስኮት አሻግራ ውጭ ውጭውን እያየች ።

“ኢያቴ ቅድመ ኢያቴ ብዬ የምጠቅሰው የትውልድ የታሪክ ሰንሰለትና ትውስታ የለኝም ። በዚች ምድር በቅለው የጠፉ የምድሪቱ ሰዎች መሆናቸውን ባውቅም ምድሪቱ ለነሱ አልሆነም እንዳለች ወይም አትሆንም እንደ ተባለ ሁሉ በረከቷን ነፍጋቸው እንደ ጫሩ እንደጣሩ ያለፉ ናቸው ። አለኝታነቱንና ጣሙ ን በውል የማልናገርለት እንካሳው አባቱ እንኳ አገሬ ለሚላት ለዚች ምድር ሙሉ ፈቃዱን ብቻ ሳይሆን ከደሙ አፍሶ ከአጥንቱ ቱስክሶ ጥቃ ትዋን ሊገፍ እንደ ተጋረደላት ሞቅ ሲለውም ሲከፋውና ችግር ሲጐነትለው ሲያነበንበው እሰማ ነበር ። ከጠላት ጐን ተሰልፈው መሪና ፊታውራሪ የነበሩ ግልጽ ጠላቶች ውለታ የዋሉ የውስጥ አርበኞች ተብለው ሲታቀፉ እሱና መሰሎቹ መገፋታቸውን እንዳማረረ ሰብአዊ ሞቱን ለብ ሷል ። እኛን ግን አራቆተን ። እርሾ የሌለው ሕይወት እን ድንቧጥጥ አጋለጠን ። እንቅጥቃጭ ዝርያ ። ” አለች ራሷን በጥላቻ ።

ምንቴም የጣደችውን ጀበና አውርዳ ከረኮቦትዋ ፊት እንደተሰየመች ሲስተር ፋናዬ በጣቶችዋ መሀል ሰንቅራ የያዘችው ሲጋራ ሳታጨሰው ራሱን እያከሰመ አመዱ ሲወድቅ አልፎ አልፎ እያስተዋለች መለስ ቀለስ እያለች የምታወራላትን በአንክሮና በተመስጦ ታደምጧ ጣታለች ። በውስጧ ግን የሲስተር ፋናዬ አባባልና አባባ ልዋ ያተኮረበት ሀሳብ የብዙዎቹን ችግረኞች ወገኖችን አላግባብ መጐሳቆል በመቃወም የወገናዊነት ቁጭት ያሸመቀ ሆኖ ተሰማት ። ታዲያ እሷን ለዚህ ሁኔታ ለይቶ ምን በቁጭት እንዳስታጠቃት ግን ሊገባት አልቻለም ። ማወቅ ከምትሻው ጭብጥ እስክትደርስ የምትሰማውን ሁሉ እያሰላሰለች ማድመጧን ወያደች ። ለአፍታ ያህል በዝምታ ውጭውን እያየች በመቆምዋ የወረደውን ሁለ

ተኛ ቡና ቀድታ ሰጠቻትና እሷም መጠጣት ጀመረች። በህይወቷ ማለዳ የገጠማትን ጐስቋላ ገድ ለመናገር ሲስ ተር ፋናዬ መሰናዶቷን ተረድታለች ።

ሁለቱም ሴቶች በዚያ የልደታ ምሽት ልባቸውን ገልጠው ቁስላቸውን አንዷ ለሌላዋ ለማሳየት ወደው ሲጨ ዋወቱ የውጭውን ጨለማ የዳጎሰ ነበር ። ከመጋረጃው በስተጀርባ ከአልጋው አጠገብ ያለው የራስጌ መብራት የሚፈነጥቀው ብርሃን በመጋረጃው የታገደ ቢሆንም እጅግ ደካማ የሆነ ጸዳል ፈጥሯል ። ወዲህ በእንግዳ ማረ ፊያው ክፍል የበራችው ክብ ሻማ ወርቅማ ቀለም ያጠለቀ ነበልባልዋን ሽቅብ እየሳየች ራሷንና በአካባቢዋ ያሉትን ቁሳቁሶች ታሳያለች ።

ጥቂት የብርሃን ጨረሮች ያረፉባቸው ልዩ ልዩ እቆች በነጸብራቃቸውና በጥላቸው ቅርጽና ምስል ፈጥ ረው ኪነ ጥበባዊ ስሜትን ይስባሉ ። ከኮርኒሱ ጋር ተጠ ላልፎ በተሰራለት አረንጓዴ ገመድ ላይ እየተሳበ ሰፊና ወዛም ቅጠሎቹን እያበራከተ የለመለመው ሀረግ ጫፉን ከሶስት አቅጣጫ ወደ ታች አውርዶ የምሽት ምግቡን አክስጂን ይሻማል ።

በሞቀ ጭውውት ላይ እንዳሉ የመድፍ ፍንዳታ ይሁን የነጐድጓድ ጩኸት ለይተው ያልተረዱት ከባድ ድምጽ ወደቀባቸው ። ምንቴም ሆነች ፋናዬ የድንጋጤ ጩኸት ጮኹ ። ድምጹ ከቤት ሳይሆን ከውጭ መሆኑን ነፍሳቸው መለስ ሲል አውቀው ተከታትለው ወጡ ። በእርግጥም ችግሩ ከጐረቤት ነበር ።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ለሚጀመር የግብዣ ጥሪ ለመሰናዳት ሲል በጊዜ ወደቤቱ የተመለሰው አስራት ማንደፍሮ በጩኸቱ ነውጥ ተስፈንጥሮ ወጥቶ የገዛ ቤቱን

ራቅ ብሎ ሲያይ አገኙት ። ሲስተር ፋናዬና ምንተስኖት
ከአጠገቡ ደርሰው ድምጹ ከምን እንደ ተፈጠረ ፤ እሱም
ምን እንደሆነ ጠየቋት ። ከወገቡ በላይ ካኔቴራ ለብሶ በእ
ግሩም ጫማ ያላጠለቀ በመሆኑ ከብርዱ ላይ የቆየው
አካሉ እንደመንቀጥቀጥ ሲል ምንቴ የደረበችውን ጋቢ
ከላይዋ ገፋ ትኮሻው ላይ ጣለችለት ። ምን እንደተፈጠረ
ያየው አለመኖሩንና ጩኸቱን ሲሰማ ከእንቅልፉ እንደ
ባነነ ዘሎ እንደወጣ ነገራቸው ። የጅ ባትሪዋን ከቤት
አምጥታ ወደቤቱ አቅጣጫ ስታመራ አስራት ማንደፍሮ
ቀደም ብሎ ባትሪውን ከፋናዬ ተቀብሏት ወደ ተከፈተው
ጨለማ ቤቱ ገባ ። ተከትለው ገቡ ። ከመታጠቢያ ክፍሉ
ከባድ የውሀ መፍሰስ ይሰማል ። ይኼኔ አስታወሰ ። እንዲ
ሞቅለት የለኮሰው የውሀ ማሞቂያ ባላወቀው ምክንያት
መፈንዳቱን ጠረጠረ ። በእርግጥም እንዳሰበው ፍንዳታው
የማሞቂያው ነበር ። የማሞቂያውን የኤሌክትሪክ መስ
መር መቆጣጠሪያ አጥፍቶ ከደጅ ያለውን ዋነኛ የኤሌክ
ትሪክ መቆጣጠሪያ ሲመልሰው የሳሎኑና የራስጌ መብ
ራቱ በራ ።

አሥራትም ድንጋጤው ሲለቀው በቤቱ ውስጥ ያሉ
ትን ጉረቤቶቹን ላደረጉለት እርዳታ እያመሰገነ እንዲቀ
ቀመጡ ጋበዛቸው ። ባትሪዋን ከጁ ተቀብላ ያልተጫ
ማውን እግሩን እያየች ቀድማ ልትወጣ የተዘጋጀችው
ሲስተር ፋናዬ አስተያየቷን አጠንክራ ቆም እንደ ማለት
ስላለች አሥራት ማንደፍሮም ሆነ ምንቴ ዐይኖቻቸው
ቁልቁል ከእግሩ ላይ አረፉ ፤ አውራ ጣቱን እንቅፋት አን
ጉዶ ጥሎት ኖሮ ደሙ እየፈለቀ ይፈሳል ። አልኮል እንደ
ሌለው ሲነግራቸው ሹራብ ደርቦ ነጠላ ጫማ አጥልቆ
እንዲመጣ ነግረው ሴቶች ተከታትለው ወደ ቤታቸው
ተመለሱ ። እንደተባለው ለብሶና ተጫምቶ በአራት

አመት ጉርብትና ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የጉረቤቱን
በር ለማንኳኳት እጁን ሰነዘረ ።

ከመርዘምዋ የመቅጠንዋ ፤ ከመልኳ ክፋት የፊቷ
አለመፈታት ፤ እያስጠላው ነገረ ሥራዋ ሁሉ የሴት ወግና
ወዘና የሸሸው ሆኖ እየታየው ሲስተርን ይጠላት ነበር ።
ሲስተር ፋናዬ ሰላምታ የማትሻ ሰላምታ የማትሰጥ አስተ
ያየቷ ዘወትር እንደ ክረምት የጠቆረና የከበደ በመሆኑ
ደፍሮ የተጠጋት አላየም ። እሱም አልሞከረውም ። ስት
ወጣና ስትገባ የመስኮቱን ብርሃን ለአፍታ ጋረድ አድር
ጎት የሚያልፈውን ቁመናዋን ናየ ቁጥር ለጥቂት ደቂ
ቆች በጥላቻ ስሜት ያስባታል ። ሠራተኛ መሆንዋን
የጠረጠረውም በሠራተኛ መውጫና መግቢያ ሰዓት ስት
ወጣና ስትገባ በማየቱ ነው ። ውሎዋን ውላ በርዋን ከፍታ
ከገባች በኋላ ሌላ ንጋት ሌላ ቀን እስኪያበስር ኳበርዋ
በስተጀርባ መሰወርዋን ስለሚያውቅ ትገርመዋለች ።

አንዳንዴ የሚሰራው ኖሮት ወይም አረፍት ፈልጐ
ከቤት ያመሸ እለት ፋጨቷን እንጉርጉሮዋን ከወዲያ
ወዲህ ምልልስዋን ይዳምጠዋል ። ጠባብና ብዙ ብር
የሚከፍሉባት ቤታቸው በብሎኬት ግድግዳ የተሠራችና
እስከጣራው ድረስም የገጠመ ባለመሆኑ እንኳንስ ንግግር
ጠንከር ያለ የሆድ ጉርምርምታን ከወዲያም ከወዲህም
ላዳመጠው ታሰማለች ።

ብዙ ጊዜ በግድግዳው ዘልቆ በሚወጣው አሰልቺ
ሙዚቃና የሬዲዮ ድምጽ እየተበሳጨ ኮቱን አንጠልጥሎ
እንደ ወጣ አድሮ ወደ ሥራ የሄደበት ጊዜም ነበር ።
አራት ዓመታት በጉርብትና ሲኖር ባያት ጊዜና ድምጿን
ሲሰማ ምን ትሆን ሴትዮዋ ? ምን ይሆን ገመናዋ ? የሚ

ለው ጥያቄ በህሊናው ብልጭ ብሎ ድርግም ሲልበት ኖሯል ።

ችክ ይልበት የነበረው ፤ ቀኑንም ማታውንም በበዓሉም በአዘቦቱም የምታዳምጠውን የክራር ዘፈን ግን ቢጠላውም ቀስ በቀስ ጥላቻው ሳያግደው በውስጡ ሰርጎ ስሜት በመዝራቱ በቅና አቀባበል እየለመደው መጥቷል ። ስርቅርቅ የሚለው ፋጨቷንም ነቅቶ ማዳመጥ ጀምሯል ። አስራት ማንደፍሮ በዚህ ልማዷ እንደ ታዘባት የካሣ ተሰማን “ ፋኖ” ዘፈን እንደምትራበው እንደምትረካበት አምኗል ። “ መንፈሷ ፋኖ ሆኖ በርቀት የሚሰደድ የሚንከራተት እየመሰለው አንዳንዴ እሷነቷን በተለያየ ኑሮ ውስጥ እየቀረጸ ያያታል ። የዚያ ግቢ አኗኗር ለማኅበራዊ ግንኙነትና አንድነት እምብዛም እድል ስለማይሰጥ ሁሉም በየቤቱ ገለልተኛ ሆኖ ይታያል የቅርብ ሩቅነት ይጐላበት ነበር ።

ከሁለት ዓመት ወዲህ የሚሰማው ድምጽና ኮቴ ግን የአንድ ሰው መሆኑ ቀርቶ እየተበራከተ ቤቱ በሰዎች ንግግር ሞቅ ደመቅ ብሎ ሰምቶታል ። በደረሰበት ችግር ሳቢያም የመጣችውንም ሴት ምንተስኖትን በአጋጣሚ አያት።

በሩን አንኳኩቶ ፤ ትንፋሽ የሚጋብዝ ድምጽ ከሰማ በኋላ ገፋ አድርጎት ዘለቀ ። የእግሩ ደም አወራረድ ምን ጣፉን እንዳይበክለው በማሰብ ከበሩ አጠገብ ቆመ ። ቁራጭ ፕላስቲክ የእግር ማሳረፊያ ካነጠፈችለት በኋላ ከሶፋው ላይ ተቀምጦ የሚደማውን እግሩን ዘረጋላት ። በተቀላጠፈ ሁኔታ በአልኮል ጠራርጋ ፀረ ተውሳክ መድኃኒት ነስንሳ ሥርዓት ባለው ሁኔታ በፋሻ አውራ ጣቱን ጠምጥማ ስታበቃ ለተደረገለት እርዳታ አሁንም ከልቡ

አመሰገነ ። ወዲያውም የሕክምና ባለሙያ እንደሆነች ጠረጠረ ።

ቀደም ሲል የተጣደው ጀበና ከከሰሉ ምድጃ ላይ እንደ ተንጠለጠለ እንፋሎቱን ፍላት እየገፋው ይተፋ ስለነበርና ዐይኖቹ ክፉኛ ሲያርፍበት ስላየች ምንቴ እንዲጠጣ ጋበዘችውና ከተነሣ በኋላ ተመልሶ ተቀመጠ ። ዱቄት ቡና ጨምራ አፈላችው ። የተከፈተው ባለቀለም ቴሌቪዥን ስለ ውሃ ውስጥ እንስሶችና ተክሎች ያሳያል ። ቴሌቪዥኑ የተቀመጠበት ቡፌ የእንጨቱ መልክና አሠራሩ ኳማሩ በቀር በውስጡ ያለው ዕቃ ስለማይታይ አስራት ያየው ነገር አላነበረም ። ከመጽሐፍ መደርደሪያው አጠገብ ከተቀመጠው ጥቁር አንገተ ረጅም ገንቦ ውስጥ የታዩት እምቡጥና የፈኩ ጽጌረዳዎች እየማረኩት አሁንም አሁንም ያያቸዋል ። ፊት ለፊት ከግድግዳው ላይ የተሰቀለው የልጅ ስዕል ልብ ይመስጣል ። ከዐይኖቹ የወረዱ የእንባ ጠብታዎች ጉንጮቹ ላይ ተቁተው ውስጣዊ ቅሬታውን ምናልባትም ብቸኝነቱና ፍቅር ወይም እንክብካቤ ማጣቱን ለተመልካች እንደሚናገሩ ተረጐመ። ከበሩ አጠገብ ንጹህና አነስተኛ አልጋ እንዳየው ሁሉ ወፍራሙ መጋረጃ በከፊል በተገለጠለት ክፍል ውስጥም የተዘረጋ አልጋ ታይቶታል ። ሌላም መጻሕፍትን የተሸከመ ጠረጴዛ በማየቱ የሴቶቹን ምሁርነት ሊጠራጠር አልፈለገም ። ቡናውን እየጠጣ ባደረገው ጭውውት ውስጥ የፋናዬን የህክምና ባለሙያነትና የምንተስኖትን ሥራ አጥነት ተገንዝቧል ። ብዙም ሳይቆይ አመስግኖ ተሰናብቶ ወጣ ። ለሌላ ያሰበው ምሽት ያሳለፈውን አስደንጋጭ ሁኔታ ጥሎበት ከቤቱ ቢያሳድረውም በዚሁ ሳቢያ ደግሞ ከጐረቤቶቹ ጋር መተዋወቁ ደስ ብሎታል ።

ምንቴና ፋናዬ በሰከነ መንፈስ ረጋ ብለው የጓሊት በትዝታ ተመልሰው የጀመሩትን ጨዋታቸውን ለመቀ ጠል ስለፈለጉ የውሎውን ለውጠው የሌሊት ልብሳቸ ውን ለብሰው ጸጉራቸውን እያበጣጠሩና እየጠቀለሉ ካጠ ገባቸው ካለው የከሰል ምድጃ ሙቀት እየተዝናኑ ቀደም ሲል እንዳደረጉት ሁሉ የሳሎኑን መብራት አጥፍተው ደብዘዝ ባለ ብርሃን ውስጥ ተቀምጠዋል ።

ምንቴ ፀጉሯን አበጣጥራ ጠቅልላ ጋቢዋን ለብሳ ጋደም ብላ ለመስማት ተዘጋጅታለች ። ሲስተር ፋናዬም እንዲሁ የጸጉሯን ሥራ ጨርሳ ሻሽዋን አስራ ጋቢዋን በረ ኸርሙ ተጎናጥፋ እንደገና ጨዋታዋን ለመጀመር ፈል ጋለች ። ቀልቧ ግን የተንጠለጠለበትና የምትሻው ነገር ስለ ነበር ዐይኖቿ በተለያዩ አቅጣጫዎች ሲማትር ቆይቶ ከመቀመጫው ስር ወድቆ አገኘችው ። በዚያ ከባድ ድምጽ ወቅት ሲጪጪኹና ተጣድፈው ሲወጡ ወድቆባት ነበር። የሲጋራዋን ፓኬትና ክብሪቷን ከጠረጴዛው ጫፍ ላይ አስቀምጣ ተመቻችታ ቁጭ አለች ።

“ ከዚህ በኋላ ጨዋታዬን የሚያቋርጠኝ ነገር ባይ ፈጠር እወዳለሁ ” አለቻት ምንቴን ከተኛችበት መለስ ብላ እያየቻት ።

“ እኔም ባይመጣ እወዳለሁ ” ብላ ትራስዋን ለት ከሻዋ ጭምር ከፍ አድርጋ ተንተርሳ ፊቷን ወደ ሲስተር አቀናች ። ልምዷ ነውና በተለይ ደግሞ ከሕይወቷ ገመና እየቀነጠረች ስትናገር ወይም ስታሰላስል ማጨስ ስለም ትወድ ገና ወጓን ሳትጀምረው ሲስተር ሲጋራዋን አቀጣ ጠለች ።

“ ምነው ፋኑ በበዛ መጠን ጤንነትሽን ይጎዳዋል እስቲ ተይው ” አለቻት ፍላጎትዋን መጋፋቷን እንደ

መሰቀቅ እያለች ። ሲስተርም ፈገግ ብላ አደመጠች እንጂ ማጨሷን አልተወችውም ።

“ ሰው ራሱን ለራሱ የሚሰስትበት ምክንያት ይኖ ረዋል ። እድሜውን አራዝሞ ለመኖር ልዩ ልዩ ጥረት የሚ ያደርግበት የሚያጓጓው ወደ ኋላ የሚያሳስበው ነገር ይኖ ረዋል ። እኔ ግን ለኔ የምሳሳ አይደለሁም ። የሕይወቴ ማጠር ቢያስደስተኝ እንጂ አይከፋኝም ። እኔ ለእኔ ደንታ እንደ ሌለኝ ሁሉ ለሰውም እንደዚሁ ነኝ ። የምጠብቀው ወቅ ትና አጋጣሚ ሠምረው እስካገኛቸው ድረስ ብዬ በሰው መሀል እኖራለሁ ። እልፍ አእላፍ የሰዎች የኑሮ ውጣ ውረድ ጥረት ተደጋግፎ ተጠላልፎ በሚገኝበት ትርምስ ውስጥ እያለሁ እርግጠኛው እኔነቴ ግን በሰፊው የብቸኝነት ምድረ በዳ እየተቃጠለ ይራመዳል ። አንዳ ንዴ የሚያጋጥሙ ለየት ያሉ ነገሮች ይገኙና እንደ መደገፊያ እንደመመርኮዣ ህሊናየ ይቀበለዋል ። ሆነና መኩሪያን አገኘሁ በመኩሪያም አንቺን ማግኘቴን ግን ግምት ሰጥቼዋለሁ ።” አለች ቀደም ሲል በተናገረችው አባባል ምንተስኖት ቅር እንዳትሰኝ ለማድረግ እንደገና ፊቷን ፈገግ አድርጋ “ ከሁሉም ከሁሉም አንቺን ማግ ኘቴን ወድጄዋለሁ ፤ ከማንም ይበልጥ ትረጂኛለሽ ታዝኚ ልኛለሽ ምናልባትም የማምንበትን ታምኛለሽ ብዬ እገ ምታለሁ ። ” ብላት ሲጋራዋን ለመተርኮስ ስትንጠ ራራ ምንቴም በጭንቅላትዋ ወዝዋዜ ባለችው ሁሉ መስማማትዋን ገለጸች ።

“ እንደ ነገርኩሽ ” ከማለቷ በር ተንኳኳ ። ሁለቱም ብስጭት ብለው ጆሮዋቸውን አቆሙ ። ተደገመ ። ሲስተር ፋናዬ “ ማነው ” እያለች ወደ በሩ ተጠጋች ። በድምጹ ስለለየችው ከፈተችለት ። እንደ ተለመደው በግራ በቀኝ እጁ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ፍራፍሬ ይዞ ገባ ። ሲስተርና

ምንቴ የጀመሩት ጨዋታ ለሁለተኛ ጊዜ በመኩሪያ መምጣት ከፍላጐታቸው ውጭ ተቋረጠ ።

የደበዘዘውን ብርሃን ዐይኑ ስላልለመደው ጨለማው ከብዶ ተሰማው ። ሆኖም ምርጫቸውን መጋፋት አልፈለገምና በዚያው ሁኔታ ሰላምታ ሰቷቸው ምንቴ ከተኛችበት አልጋ በግርጌ በኩል ተቀመጠ ። የቀረበውን የምድጃ እሳት ወደ መሀል ገፋ አድርጎ አራቀው ። በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከተነጋገሩ በኋላ ንግግራቸው ወደ አንድ አቅጣጫ እየተሰባሰበ መጣ ። ሰሞኑን እየተመላለሰ ባየውና በአረጋገጠው ሁኔታ የውብሸት እንዳይላሉ ጤንነት ከሚያሳዝን ደረጃ ላይ መድረሱን ነግሮአቸዋል። በጭንቅላቱ ውስጥ በደረሰው ደም መፍሰስ ከፊል አካሉ ሽባ ሆኖ ሆስፒታል ከገባበት ዕለት ጀምሮ የመናገር ሙከራም እንዳላደረገም አውቀዋል ።

መኩሪያ አቀርቅሮ በጁ የያዘውን የክር ቁራጭ እያፍተለተለ ፤ ስለ ውብሸት እንዳይላሉ ጉዳይ ሲናገር ፤ ከነሱ ጋር በጋራ ምክክርና ድጋፍ ሊያደርገው የሚሻው እቅድም እንዳለው ሲያስታውቃቸው ፤ ምንቴ ተዝናንታ ከተጋደመችበት አካሏ ኲምትርትር ብሎ ሲጠነክርና ከልቧ ሥር እንደ እሳት የሚፈጅ ስሜት ሲንቀሳቀስ ተሰማት። ሲስተር ግን የሚቀጥለውን ሀሳብ ለመስማት ወደ ኋላ ተደግፋ ዝም ብላለች ። ለጥቂት ጊዜ መኩሪያም ያቀደውን እቅድ እንዴት እንደሚያስረዳቸው እያሰላሰለ ዝም አለ ።

ለመኩሪያ ባላት መውደድና አክብሮት እንጂ በዚያች ቅጽበት ብዙ የምትናገራቸው የመረሩና ቋስ የቋጠሩ ቃላት ነበሯት ። የሱን ሀሳብ ለማስጨረስ ስትል አፏን ደም ደም እያላት ዝም ብላ እንደ ሲስተር ጠበቀችው ።

ረጋ ባለው አንደበቱ አዘኔታ እንደሰረገበት በሚያስታውቅ አነጋገር ከጥንቱ ከጥዋቱ የተደረገውን ቂምና ጠላትነት ያተረፈውን ግንኙነት ነቅፎና የኋላ ኋላ ባልታለመ ፤ ባልተጠረጠረ አጋጣሚ የሚገርምና የሚያሳዝን የሚያስደንቅ ውጤት ፤ ማየታቸውን አስገንዝቦ ከዚህ በኋላም ደግሞ ችላ ተብሎ ሊታለፍ የማይገባው ተመካከረው መልክና መንገድ የሚያስይዙት እጅግ ከባድ ነገር እንዳለ ደግሞ አስገነዘባቸው ። ቀና ብሎ ፈርጠም ባለ አነጋገር ፤ ውብሸት እንዳይላሉ ቢያውቃትም ፤ ውዴ ግን አባቷ መሆኑን የጠረጠረችበት አንዳችም ፍንጭ እንደሌለ ገልጾ ይህ ሰው ከከፋ ሁኔታ ለመድረስ አመቺ ችግር ላይ መሆኑን አስገንዝቦ ያ ከመሆኑ በፊት ግን ልጇን ማስተዋወቅ እንዳለባቸው ከገለጸ በኋላ የሚኖራቸውን አመለካከትና አቀባበል ለመስማት ሲል እንደገና አቀርቅሮ ጠበቃቸው ።

እልህ አንቋት መናገር አቅቷት ነበርና ከተጋደመችበት ተነስታ እግሯን ከነጩ ድብዳብ ላይ አሳርፋ አንገቷን ደፋ አድርጋ እንባዋን ለቀቀችው ። መኩሪያ አንጀቱ ተላወሰ ። ትከሻዋን አቀፍ አድርጎ ፤

“ በደልሽን አውቀዋለሁ ። ብሶትሽ ይሰማኛል ፤ ሆኖም ለልጅሽ ስትይ ግፉን ለፈጣሪ ፍርድ ትተሽ በይቅርታ ሁኔታዎችን መታዘብና መመልከት አለብሽ ። በይበልጥም ለልጅሽ እዘኝላት ። የማታውቀውን አባቷን እንደ ምትናፍቅ ልታውቂው ይገባል ።” አላት ።

“ ነፍስ ገዳይዋ ፤ ጠላትዋ እንጂ አባትዋ አይደለም፤ ኖሮም የጠቀማት የለም ቢሞትም የሚጐዳት አይኖርምና መስማትዋን አልደግፈውም ” አለችው ሲቃ ባበላሸው ድምጿ ፤

" ከህሊና ጭንቀት ከስውር ናፍቆት ልናድናት ኃላፊነት አለብን ፤ ከቋሳና ከበቀል አኳያ የምናነጻጽረው ሁኔታ አልመሰለኝም ። "

" በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ማንነቱን ብታውቅ የበለጠ ድንጋጤና የመንፈስ ጭንቀት ያድርባታል ፤ ትረበሻለች ። ከዚህም ሌላ አባት የሚለውን ክብር ስም እንድ ትሰጠው አልፈልግም ። "

" የሷን ስሜት በአንቺ ፍላጐት ውስጥ አካተሽ ለመወሰን የሚያስቸግር መሰለኝ ። "

" እውነተኛውን ሁኔታ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እንድታውቀው ቢደረግ ከደረሰባት እንግልትና ግፍ አኳያ የኔኑ የመሰለ ወይም የበለጠ አቋም ሊኖራት ይችላል "

" ይሆናል ብሎ ሙሉ በሙሉ ለመደምደም ያዳግታል " አለ መኩሪያ ።

" እንዴት "

" ከዚህ የተለየ የራሷ የሆነ አመለካከትና ውሳኔ ሊኖራት ይችላል ብዬ ነው"

" በአሰቃቂ ሕመም ስትሰቃይ የመድኃኒት መግገ የነፈጋትን ሰው ፤ ሞተች ወይስ አለች ብሎ የደቂቃ ትውስታ ያላደረገላትን ሰው ፤ የኋላ ኋላም ገረዱ ሆና ጉልበቷን የመጠጠውን ሰው ፤ አባትሽ ሆኖ ተገኘ ብትባል የሚሰማት ስሜት ለመገመት የሚቸግር አይመስለኝም ። ስለዚህ ልጄን ለአእምሮ ጭንቀት መዳረጉን አልደግፈውም ። " ምንቴ ንግግሯ ቁጣና ምሬት አዝሎ ነበር ።

ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሆነ ።

" እርግጠኛውን ነገር ሰምታ የራሷን ውሳኔ እንድ ትወስድ ለምን ዕድል አንሰጣትም"አለ መኩሪያ ቀና ብሎ፤

" ይህንን ስምና ክብር ሊያገኘው ቀርቶ ሊሰማው አልፈቀደውም ። አባቷ መሆኑንም ላለማወቅ እገደዳለሁ ።" አለችው ። ግትር አቋሟን ለማለዘብ የሚችልበትን ሀሳብ እያሰላሰለ ፤

" እንደሚሰማኝ " አለ ። ረጋ ባለ አነጋገሩ ፤

" እንደሚሰማኝ እምቢታሽ የልጅቷን መብት እንደ ማፈንና እንደ መንፈግ እቆጥረዋለሁ ። የፍላጐትዋ ግፊት ጠንክሮ በሚመጣበት ወቅት በተለያየ ዘዴ ልትደርስበት የምትችለውን ሁኔታ በቁጥጥራችን ውስጥ ባለበት ጊዜ በሥርዓት ማስረዳት ብንችልና ከዚያ በኋላ ለሚኖረው ሁኔታ ውዴ ከማንም ተጽዕኖ ነጻ የሆነ ውሳኔዋን ብታደርግ አሁንም የተሻለ መሆኑን ብትረጅልኝ እወዳለሁ ። " አለ መኩሪያ በዚህ ጉዳይ ላይ ንግግሩን ላለመቀጠል እንደ ወሰነ በሚያመለክት አባባል ወዲያውም በዚህ ሁሉ ንግግር መካከል በጨዋ አድማጭነት የሁለቱን ምልልስ ስታደምጥ ወደ ነበረችው ሲስተር ፋናዬ መለስ ብሎ

" አስተያዬትሽን ብትሰጪን ከሁለት አንዳችን ልንሸነፍ እንችላለንና ምን ታስቢያለሽ ሲስተር " አላት ወደሷ አቅጣጫ እየተመለከተ ። ሲስተር ፋናዬም ሀሳብዋን ለመስጠት ፈቅዳ ቀጠለች ።

" አስቸጋሪ ነው የሰውን ስሜት ሙሉ በሙሉ ለመረዳት አለመቻል አለ ። አስተያየት ለመስጠት ግን እወዳለሁ ። ለኔ የተሰማኝ ለምንቴ የሚሰማት ላይሆን ይችልና ፤ ወይም አንተ የተሰማህ ለኔ ስሜት ያልሰጠኝ ይሆንና የከበደው ላይከብድ የቀለለው ላይቀል ይችላል ።"

‘ሆኖም’ አለች፤“ሆኖም በቅድሚያ ትክክለኛውን ታሪክ
ስምታ ውዴ የአባቷን ማንነት ማወቅና ከመሞቱም በፊት
ማየት እንዳለባት እደግፋለሁ ። ይህንን ስል ፤ ሰውየው
የአባትነት ክብሩም ሆነ ስሙ የሚገባው ሆኖ ሳይሆን
ውስጥ ውስጡን የሚያብሰለስላትን ጥያቄ ለመቅጨትና
ከስውር የመንፈስ ሕመም ለማዳን ለውዴ ህልውና ስል
ነው ። ደግሞም የኛን ስሜትና አቋም እንድትቀበል ጫና
ማድረጉም አይገባም ። ነገሮችን አመዛዝና መረዳት ከም
ትችልበት እድሜ ላይ ስላለች ስለምትወስደው አቋም
ወይም ውሣኔ እኛ ልንነጋገር አይገባንም እላለሁ።” ሲስ
ተር እንጋገሯ ደረቅ ብሎ ነበር ።

“ ምንቴ ” አላት እንደገና ትከሻዋን ደግፎ ወደ
ሰውነቱ እያስጠጋት “ ልጅሽ የኔን አጐትነት ሳትጠራ
ጠር በተቀበለችበት የዋህነትዋ አባቷን የኔን ወንድም
ማለት ነው ፥ እንዳሳያት አለዚያም ቁርጡን እንድነግራት
ሳትሰለች ትጠይቀኛለች ። መልኩን ለማየት አንደበቱን
ለመስማት ትጓጓለች ፤ በአእምሮዋ ውስጥ በተለያየ ምስ
ልና አቋም እየሳለች ታልመዋለች ። በመንገድ ላይ የም
ታየውን ሰው ሁሉ አባቴ ይሆናል በሚል ጥርጣሬ ታተኩ
ርበታለች ፤ ቤተሰብዋን በተመለከተ ከጓደኞችዋ ጋር የምት
ካፈለው ሀሳብ እንደሌላት ነግራኛለች ። የተሰበረ መን
ፈስ የተሸማቀቀ ህሊና አትርፋለች ። ይህ የመንፈስ ስቃይ
የተሸሸገ ሕመም ይፋ የአካል ችግር የማይሆንበት ምክ
ንያት አይኖርም ። ለሷ ጤንነትና ሕልውና ከማንኛችንም
የበለጠ የምትጨነቂው ለሷም ስትይ መከራ ያየሽው አንቺ
ስለሆንሽ ሌላውን ነገር ሁሉ አዳምረሽ ሳታይው ይህን
የጠቀስኩልሽን ነጥብ ነጥለሽ መርምሪው ። ” አላት ።
አባባሉ ይበልጥ ወደ ልመና ያደላ ነበር ። በቁጣ
ነቅቶ የነበረው አካሏ እንደገና በሀዘን ጥውልግ ብሎ የመ

ኩሪያን ትከሻ እንደ ተደገፈች በዝምታ ህሊናዋን እያደ
መጠች ቆየች ። ከትከሻው ላይ ቀና ሳትል ስብር ባለ
ድምጽ ፤

“ እሺ ያልከው ይሁን ። ” አለችው መኩሪያን ።
መኩሪያም በደስታ ግንባሯን ስሞ በሁለት እጆቹ ጠበቅ
አድርጎ አቅፏት መከራና ችግርን በአሸናፊነት ያለፈች
መሆኑን አውቃ ልትደሰት እንደሚገባት እያስገነዘበ አጽ
ናናት ። ወዲያውም እጅዋን ጐትቶ ከግንባሩ ላይ ያለውን
ፍንክትና ጠባሳ አስዳበሳት ።

ለዚህ የታሪክ ደረጃ የደረሰውን ሁኔታ ገና ከመጀመሪ
ያው ይቃወም እንደነበርና በዚህም ምክንያት በተነሣው
አለመግባባት መኩሪያና ውብሸት እንዳይላሉ ተደባድ
በው መኩሪያ ሲፈነክት የውብሸት ጥርሱ እንደ ተሸረፈ
እየሳቀ ነገራት ። የዚያች የመድኃኒት መግገ ማዘዣ ወረ
ቀት ሆን ብሎ መደበቅ የቋጠረው ቋሳ በሕሊናዋ ውስጥ
እንደሚንቀሳቀስ መረዳቱን ቢያውቅላትም ዕድል ለሞት
ጭዳ ያላደረገቻትን ሕጻን አባትዋንና ገዳይዋን በአንድ
የአካል ቁመና ላይ ለማየት ብትችል የሷን ሥቃይና እን
ግልት የበለጠ ልትመዝንላት እንደሚያመቻት በማረጋ
ገጥ ውዴ የወላጆችዋን እርግጠኛ ታሪክና ማንነት እንድ
ታውቅ በመፍቀዷ እንደገና ግንባሯን በመሳም ደስታውን
ገለጸላት ። ሲስተርም ሀሳቡን በቀና መንፈስ በመቀበልዋ
አመሰገነቻት ።

ይህንን ለውዴ ብቻ የተጋረደና የተሰወረ ምስጢር
ለመንገር ዘዴና ስፍራ መምረጥ እንደሚያሻው ብዙ ከተ
መካከሩ በኋላ በቅድሚያ የወ/ሮ ሙሉን አያትነት የምን
ተስኖትን እናትነት ከተገለጸላት በኋላ የውብሸት እንዳይ
ላሉን አባትነት ለማስረዳት የሚያመች መሆኑን አመኑ

በት፡፡ምንም እንኳ ምንተስኖት ከዓመታት የአእምሮ መደ ንዘዝ በኋላ በነቃችባት ቅጽበት ልጄን ብላ ውዴን ቢያ ቀርቡላትም ለውዴ የተነገራት ታሪክ ግን የጭንቀትዋ ማስታገሻ እንድትሆን ለወዲያው ጥያቄዋ መልስ እን ዲሆን የተደረገ መሆኑን ነበር ። ውዴም የምንተስኖትን የአእምሮ ሕመም በመገንዘብ የተባለውን ለመጠራጠር አልሞከረችም ። ውዴ ምንተስኖትን በእህትነቷ ፤ መኩ ሪያን በአጐትነቱ ተቀብላ ፤ የአባቷን ማንነት ለማወቅ ብዙ የምታሰላስል ነገር ግን ደፍራ ወ/ሮ ሙሉንም ያል ጠየቀች ሆኖም ከጥቂት ጊዜ ወዲህ አጐትዋ መኩሪያን እየውተወተች መልስ የምትጠብቅ ተጨናቂ ልጃገረድ ነበረች ።

ይህንኑ አስገራሚ ምናልባትም አስደንጋጭ ሊሆን ባት የሚችለውን ታሪክ ከማንኛቸውም ይልቅ መኩሪያ በእርጋታና በብልሀት እንዲነግራት ተወስኖ ኃላፊነቱ ተሰጠው ። ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ መኩሪያ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከባድ የአካል ላይ ጭነት የወረደለት ያህል ቀሎት መንፈሱም ደስታ ወሮት ነበር ። መኪናውን በዝ ግታ እያሽከረከረ በምን መልኩ ይህንን ውስብስብ ታሪክ ለውዴ እንደሚያቀርብ ዘዴ እየነደፈ ደረሰ ። የመኪናውን ጥሩምባ ሰምታ በሩን የከፈተችለት የኖረች ሰራተኛቸው ከጅዋ ላይ ያለውን ድፍድፍ አጥርታ አልተለቃለቀችውም። የግቢው ጠረን በጠቅላላ በጠላ ሽታ ያውዳል ።

መኪናውን ዘግቶ የመኪናውን ውጫዊ አካል ጐን በስ ቀና ብሎ እየተመለከተ ሳለ ንቅሳታሟ ሠራተኛቸው የውጪውን በር በመቀርቀሪያ ደንጉራ ተመልሳ ከአጠ ገቡ ቆማ ስትመለከተው አያት ።

" ምነው" አላት ፤

" አይ ጋሽ አንድ ነገር ልነግርዎት ፈልጌ ነው"

" ምን ? "

" እርስዎ ምንም ያወቁ አልመሰለኝም ፤ እማማ እኮ ሊመንኰሱ እየተሰናዱ ነው"

" ታዲያ ጥሩ ነዋ ከፈለገችው "

" መንኩሰው እኮ እዚህ አልቀመጥም ብለዋል "

" የት ልትሄድ አሰባለች"

" ደብረ ሊባኖስ ከእማማ ትልቋ ጋር እኖራለሁ ብለ ዋል "

" አማክራሻለች "

" አይ ለሰዎች ሲያማክሩ ፤ ሲያወሩ ስለሰማሁ ነው"

" ጥሩ ነዋ "

" ለምን መንኩሰው እንደሚሄዱ ያውቃሉ ?"

" አውቃለሁ "

" ለጾም ፤ ለጸሎት ፤ ለጽድቅ መስሎዎት እንዳይሆን"

" ከዚህ ሌላ ለምንድነው ታዲያ "

" እርስዎን አኩርፈው ነው"

" እኔን"

" አዎ"

" ለምን"

" ሚስት አላገባም ስላሉ "

ከማድቤቱ የሚጣራ ድምጽ ሰማችና ሠራተኛዋ 'አቤት' ብላ ትታው ሮጠች ። ድፍድፍ ማገላበጧን ረስታው የቀረች መሰሏት ሌላዋ ሠራተኛ በሚያንቃጭል ድምጿ ስትጠራት ሰምታ ነበር ። መኩሪያ መኪናውን ደገፍ

ብሎ እጆቹን ከሱሪው ሁለት ኪሶች ከቶ ሽቅብ በደመና እየተጋረደች የምትጠፋውን እየሾለከች የደበዘዘ ብርሃኗን የምትሰጠውን ጨረቃ ተመለከታት ። እየጋረዳት የሚጓዘውን ደመና እንቅስቃሴ እየተከተለ የተነገረውን ሁኔታ ማሰላሰል ያዘ ። ይህም ጉዳይ አንድ መልካም መቋጨያ የሚያስፈልገው ችግሩ መሆኑን አምኖ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በዚያ ምሽት ክብደትና ትኩረት ሰጥቶት መፍትሔ ሊሻለት ወሰነ ። ከራሱ ጋር የአጭር ቆይታ ምክር ካደረገ በኋላ በማንኛውም መልኩ ቢሆን ከእናቱ ጋር ዘወትር የሚያቋስላቸውን ነገር መቅጨት ፈለገ ። በዚህ ውሣኔው እንደሚተጋ ለራሱ ቃል እየገባ ወደቤት ቤት ዘለቀ ። የእንግዳ ማረፊያው ክፍል ተጸዳድቶ ጭርና ቅዝቅዝ ብሎ እንደ ዘወትሩ ብቸኛ ነው ። የእንግዳ ማረፊያውን ክፍል አልፎ በስተግራ ወደ፣ሚገኘው መኝታ ክፍላቸው አመራ ። በሩ ገርበብ ብሏል ። ቀስ ብሎ ገፋ አድርጎት ገባ ። አልነቁም ። ወ/ሮ ፋኖሴ መቁጠሪያቸውን በጣቶቻቸው መሀል እንደ ያዙ በቀኝ ጐናቸው ኮአልጋቸው ጠርዝ ሳይርቁ እንቅልፍ ወስዷቸዋል። በጸጥታ ቆሞ አትኩሮ ካያቸው በኋላ የናቱ እውነተኛ ፍቅር ከልቡ ሥር በናፍቆት ይሁን በአዘኔታ ብቻ ለይቶ ባላወቀው ስሜት ክፉኛ ሲላወሰበት ኩተኙበት የተሸበሸበውን ለስላሳ ጉንጫቸውን በርከክ ብሎ ሳመ ። ባንነው ሲነሱ ትከሻቸውን በተኙበት ይዞ አረጋጋቸው ።

“ ምነው መኩሪያዬ ምነው” አሉት በንጹህ ልባቸው ፤ በንጹህ ህሊናቸው የሚሉትን አባባል በድንጋጤያቸው ምክንያት ቁጣና ኩርፊያ ሳይቀላቅሉበት ።

“ደህና ነኝ አትደንግጪ ምክር ላካፍልሽ አስቤ ነው” አላቸው ከመሬቱ ምንጣፍ ላይ ኪፊት ለፊታቸው ሸብረክ ብሎ ። መንፈሳቸው እየተረጋጋ በመምጣቱ የመሰንበ

ቻውን ኩርፊያ አስታውሰው ቁጣና ግልምጫ ባንሰራራበት አባባል “ የምን ምክር ” አሉት ። መኩሪያም መቁጠሪያ የያዙትን እጆቻቸውን እያሻሸ ፈገግታ ባሳነሳቸው ዓይኖቹ እያያቸው ፤

“ እንግዲህ መደረግ ያለበትን ሁሉ እንድታስቢበት በቅርቡ ሚስት ለማግባት ወስኛለሁ ።”

“እኔማ ለዚህ ምክር ለዚህ ክብር ያልበቃሁ ነኝና ያሻህን አድርግ በል ውጣልኝ ልተኛበት ።” አሉት መላ አካላቸው ከእንቅልፍና ከድካም በአጭር ጊዜ ውስጥ ነቅቶ።

“ ጊዜው እስኪደርስ ለመጠበቅ ብዩ እንጂ ፈቃድሽን ላለመፈጸም ብዩ ቃልሽን አልገፋሁትም ። አሁንም ያላንች ምንም የሚሆን የለምና ይልቅ አስቢበት ”

“ የለም ልጄ ፤ ያንተን ኑሮ ፤ ያንተን ሕይወት ፤ ለመወሰን የማልችል መሆኑን ነግረኸኝ ልብ አድርጌዋለሁ። ብትወልድ መውለድህን ላልሰማ ፤ የወለድከውንም ላላይ አግደኸኛል ። ለነገሩ እኔው በጥረቴ እንደደረስኩበት አወላለድህም የሚያሳዝን የሚያሳፍር ሆኖ አግኝቼዋለሁ ። ይኸም ታዲያ እኔው ባለመታደሌ እንጂ ከማንም ያነሰ ዘርና ታሪክ ኖሮኝ ተንቄ አልነበረም ። ሲሆን ለመከታነት ለወገንነት ዘሬ የሚፈለግ አባቴን ጠርቼ አያት ቅድመ አያቶቼን መደርደር የምችል ነበርኩ ። ሳይሆን ቀረ ። ብቻ አሁንም ያሻህን አድርግ ቤቱንም ለቅቄልህ በቅርቡ እሄዳለሁ።” አሉት አነጋገራቸው በቅሬታ ስብር ብሎ ወደ ተሰቀለው የቅዱስ ገብርኤል ስዕል ዐይኖቻቸውን ስክት አድርገው በተመስጦ እየተመለከቱ ። መኩሪያም ይኸኔ በልባቸው ገብርኤልን እያመሰገኑ ይሆናል ብሎ ጠረጠራቸው ።

መኩሪያም ከት ብሎ ስቆ ከተንበረከከበት ተነስቶ ከግርጌ የተቀመጡትን በርጩማ ይዞ ከናቱ ፊት ተቀ ምጦ እሳቸው እየተቆጡ እሱ እያባበለ ንግግሩን ቀጠለ ። ለወ/ሮ ፋኖሴ ከልጅነት እስከ እርጅና ጓደኛቸው የሆኑትን እማሆይ ሻሸቱን አስታራቂ ይዞ ሊገልጽላቸው ያሰበውን በትክክለኛው ገጹ ያልተረዱትን የውዴን ህመም ጉዳይ ገለጸላቸው ። መኩሪያ ምንጊዜም ወሳኝና የመጨረሻ ለሆነ ቃሉ የሚምለው በእናቱ በወ/ሮ ፋኖሴ ስም መሆኑን ስለሚያውቁ ደጋግሞ " ፋኖሴ ትሙት " እያለ እንደ በፊቱ በሣቅና በገራም ጨዋታ መልክ ሳይሆን ጠንከር ብሎ ስለ ገለጸላቸው አመኑትና ሀሳቡን ሁሉ እየተገረሙ አደመጡት ። በሠራው ሥራ ሁሉ እየተደሰቱ ልባቸው በርኅራኄ ተሞላ ። ውዴን ሊያዩዋት ጓጉ በተለይም ጓደኛዬ ብሎ ያወሳላቸውን የውብሸትን ታሪክና የሚገኝበትን የጤና ደረጃ እያሰላሰሉ እግዚአብሔር ለሁሉም እንደ ሥራው ይከፍለዋል በሚለው የእምነት ጽኑ ቃል መንፈሳቸውን ይበልጥ አጠነከሩት ። ወዲያውም ልጃቸውን ጭንቅላቱን ጉተት አድርገው ግንባሩን ከሳሙት በኋላ ከጭናቸው ላይ አስደግፈውት በጣቶቻቸው እየደባበሱት ተቆጥተው አኩርፈው የከረሙበትን ሀሳባቸውን ገለጹለት ።

እሳቸውም ዛሬ ሁኔታውን በግልጽ ሲረዱት የሳቁበት ጉዳይ በወቅቱ ግን ያበሳጫቸውና ከልጃቸው ጋር ወደ መረረ ጸብ ያራመዳቸው ከውዴ ልጅነት የወ/ሮ ሙሉ እናትነት መሆኑን ሲገልጹለት ቀደም ሲል የጠረጠረው ቢሆንም ከአንደበታቸው ሲሰማውና የግላቸው በሆነ አገላለጽ ወ/ሮ ሙሉን ሲያጥላሏቸው ሲሰማ መኩሪያ እንባውን እያረገፈ ከልቡ ሣቀ ።

እጉል የነበረው ቅሬታ ተገፎ ሰላምና ፍቅር የወትሮ ቦታቸውን ሲይዙ እንደ ልጅነቱ ጊዜ ዛሬም በጉልምስናው ጸጉሩን እየደባበሱ እንዴት ያለችውን ሴት ሊያገባ እንደ ተዘጋጀ ጠየቁት ።

የሳቸውን ምኞትና ፍላጐት ጠንቅቆ ቢያውቅም ከዚህ በኋላ ተጽዕኖ ለማድረግ እንደማይከጅሉ በማመን፤ የተማረችና ሥራ ያላት ፤ ጸባይዋ ከጸባዩ ጋር የተስማማ መሆንዋን ብቻ ነገራቸው ። ይህ መግለጫው አላረካቸውም ስላለ ዘርዋን ፤ ሃይማኖቷን መልኳን ጭምር ጠየቁት ። ሃይማኖትዋ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ዘርዋም የናቱ ዘር ማንዘር በጌትነት በጀግንነት በጨዋነት በቅሎ ኮረፈበት ከአገራቸው መሆኑን ነገራቸው ። ስለ መልኳ ግን ያነሳው ነገር ባለመኖሩ እንደገና እንደሚጠይቁት አረጋግጠው ከሁሉ ከሁሉ ክርስቲያን መሆኗና ደግሞም የሳቸውን ዘርና ታሪክ ማንም የአገሬው ሰው ከሚያውቅበት ከዚያው ምድር የምትወለድ በመሆኗ በገናው ወደዷት ። የከነኮናቸውን የቀረ ጥያቄ መልኳንና ቤተ ክርስቲያን መሳም መውደዷን ሲጠይቁት ። ከልቡ ስር ፍንቅል ባለ ሣቅ ቤቱን ሞላው ። መኩሪያ የታየው ገና ሀሳቡን ያልገለጸላት ፤ ቢገልጽላትም የማትቀበሉው ልትሆን የምትችለው፤ብትቀበለውም ከተባለው ነገር ሁሉ ጋር እጅግም የማትጣጣመውን የሲስተር ፋናዬን ጸባይ ፍላጐትና ተግባር አስቦ እንደገና የተደቀነበትን ፈተና ከወዲሁ እየፈራው ሳቀ ።

የአሳሳቁን ሁኔታ አይተው ከረር ባለ ጥያቄ ፤" ክርስቲያን ሆና ቤተ እግዚአብሔር የማይሳለም ምን ዓይነት ክርስቲያን ነው ታዲያ " አሉት ቀና አድርገው ዓይን ዐይኑን እያዩት ። አንዳንዴ በሥራ ምክንያት ካልሆነ በቀር ቤተ እግዚአብሔርን እንደምታከብር አስረዳቸው ።

እንደ ጠረጠረውም ዐይኖቻቸውን ፊት ለፊታቸው ወደ ተሰቀለው የቅዱስ ገብርኤል ምስል አቅንተው የምስጋና ቃላት በይፋ አነበነቡ። ወ/ሮ ፋኖሴ የልባቸው ጭንቀት ሲበተን የከበዳቸው የቁጣና የኩርፊያ ኑሮ ከላያቸው ላይ ሲወድቅ መኩሪያ ደግሞ ወዲያው በሀሳብና በጭንቀት ተወጠረ ። እንደ ዱሮው እናቱን ጉንጫቸውን ስሞ የሌሊት ልብሳቸውን አስተካክሎ አልብሶ መብራቱን አጥፍቶላቸው ወጣ ።

የእናቱን ሀዘንና ቅሬታ ለመግሰስ ሲል መሰናዶ ያላደረገበትን ጉዳይ ከጨረቃ ብርሃን ሥር ቆሞ ወስና የውሣኔውን እፍታ ለእናቱ አቅርቦላቸው ሲደሰቱ ማየቱ ቢያረካውም ፤ የሰላም እንቅልፍ መተኛት መቻላቸው እፎይታ ቢሰጠውም ይህ የደቀነው እቅድ ሰምሮ ገሀድ የሚታይበት ሁኔታ የት የለሌ ሆኖ ራቀበት ። መኩሪያ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ላሶበው ነገር መሳኩት ሲል ልቡ በስለት የፈጣሪውን ፈቃድ ተማጸነ ። ይህን ከህሊናው ላይ እንደመርግ የተጫነ ድንገተኛ ሀሳብና ውሣኔ አቅሮት ሊተኛ አልቻለም ። ከእንግዳ መቀበያው ክፍል ሳይወጣ ለመቶ አለቃ አፈወርቅ ደወለለት ። መቶ አለቃ የምሽት ተረኛ ነበርና ከእኩለ ሌሊት በፊት እንደማይገባ ሰማ ። በመጣበት ሰዓት እንዲደውልለት መልእክቱን ሳይዘነጋ እንዲነግርለት ለወንድምየው ደጋግሞ አሳስቦ ስልኩን ይዞት ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ ።

ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ሲሆን ስልኩ አንቃጨለ ። እንቅልፍ ሸሽቶት ፍጹም በሆነ ንቃት ኮአልጋው ላይ ተንጋሎ እጅግ ዝቅ ባለ ድምጽ ሙዚቃ ያዳምጥ ነበርና ወዲያው ጥሪውን ተቀብሎ መቶ አለቃን ማነጋገር ጀመረ ። ከሰላምታው ቀጥሎ ከመተኛቱ በፊት የሆነውን ሁሉ እንደ ሁኔታው በቅደም ተከተል ዘርዝሮ አጫ

ውቶት ለዚህ መፍትሔ እንዲፈለግለትና ከደቂቃ ወደ ደቂቃ እያስጨነቀው ለመጣው ጉዳይ ምክሩን እንዲያካፍለው ጠየቀው ። መቶ አለቃም የጭንቀቱን ጥልቀት መርምሮ ከተረዳ በኋላ የሲስተርን ለየት ያለ ጸባይና የአኗኗር ስልት ከሌሎች አለመግጠም በማስታወስ ትዳርን በተመለከተ የሚኖራትንም አቋም ሳይታወቅ ይህን ግልብ ውሣኔ መውሰድና ውሣኔውንም ለእናቱ በምስራችነት በማቅረቡ መሳሳቱን አጥብቆ ነገረው። ሆኖም ካለው ሁኔታ በመነሣት በሀሳብ የተነደፈውን ሠርግና ትዳር እውን ለማድረግ ምን መደረግ እንዳለበት ተወያዩ ። ዞሮ ዞሮ ጥያቄውና ያለውን ዓላማ የመግለጹ የቅድሚያ ሥራ በመኩሪያ መጀመር እንዳለበት አስገንዝቦት ፤ ይህም ቶሎ እንዲደረግ አሳስቦት ጥቂት እንቅልፍ ለማግኘት መቶ አለቃ ተሰናብቶት ተደላድሎ ተኛ ። መቶ አለቃ ግን ከማሸለቡ በፊት በአማራጭነት የያዘው ሀሳብ ነበረውና እንደ መኩሪያ አልከበደውም ። አሰለፈች በዳኼን አሶታውሷታል ።

ምንም እንኳን በነጋታው ዕለቱ ዕለተ ታዲዮስ ቢሆንም ምሲጋናቸውን በጸሎትና በስግደት ለማቅረብ ልባቸው ወደ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን መሄድ ስለ ከጀለ ማልደው ተነስተው ለባብሰዋል ። እንደተለመደው ከሳቸው አልጋ ሥር የሳር ፍራሽዋን አንጥፋ የምትተኛው ልጅ እግሯ ሠራተኛቸው አብራቸው ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ተነስታ ወደ ጓሮ ዞራለች ። ጋቢያቸውን ከትከሻቸው ላይ እያደላደሉ መቁጠሪያቸውን በእጃቸው ላይ እየጠመጠሙ ወጥተው የመኝታ ክፍላቸውን ቆልፈው ወደ መኩሪያ ክፍል ሄዱ ። ሀሳብ ሲወዘውዘው ቆይቶ ሊነጋጋ ሲል ስለጣለው ድምጽ ባሶው እንቅልፍ ተውጦ አዩት ። አይቶ በማይጠግበው ዐይናቸው በመላ አካሉ ላይ ተመላለሱበት።በአስተኛኘቱም አንጀታቸው እንደ መላወስ ሲል

በጥቂቱ ገርበብ አድርገው የያዙትን በር መልሰው ዘግተው መቋሚያቸውን ከበሩ አጠገብ አንስተው ጸሎት እያነበነቡ ወደ ደጅ ወጡ ። የንጋቱ ብርድ ሸነቆጣቸውና አካላቸው ስብስብ አለ ።

መቋሚያቸውን በእጅጉ እየተመረኮዙ ፤ ሸቅብ ወደ አቧሬ የሚወስደውን መንገድ ይዘው ተራመዱ ። የአቧሬን የጉልት ገበያ በስተቀኛቸው ትተው እንኳን ሰው የመኪና ጉልበት የምትፈትነውን ዳገት ቁና ቁና እየተነፈሱ ወጥተው በስተግራ ቆልቆል በሚለው የእግር መንገድ ፊት ለፊት የቤተክርስቲያኑን ጉልላት እያዩ ወደዚያው አዘገሙ ። የገብርኤልን ቤተ ክርስቲያን ያደሉለታል ።

ወሬዋ በአጭር ተቀጭቶ የቀረው ሠራተኛ የወጠነችውን ወሬ ተናግራ ለማረፍ እጅግ ተቁነጥንጣ ስለነበር መኩሪያን ከእንቅልፉ ቀስቅሳ ሰዓት መድረሱን ነግራ አነቃችው ። የፊት ውሀ እየጨመረችለት ማታ የተወችውን ወሬ ለመቀጠል ጀመር ስታደርግ “ ተይው ሁሉንም አውቀዋለሁ ” ብሎ አገዳት ። እፍረትና ብስጭት የተሰማት ሠራተኛ ቁርስና ሻይ ስታቀርብለት ሁሉ ኩርፊያዋ በከንፈሯ መንጠልጠል ይታወቅባት ነበር ።

የቀረበለትን ቁርስ እንደ ነገሩ ለካክፎ ፈጥኖ ወጣ። የአካሄዱ አቅጣጫ ወደ አፍንጮ በር ነበር ። መኪናውን ከመንገድ ዳር አቁሞ ቁልቁል ወደ መንደሮቹ ውስጥ እየተጣደፈ ከገባ በኋላ የአካባቢው ሽንት ቤት ፈንድቶ ቦይ ሠርቶ የሚወርደውን ፤ የቆሻሻ ፍሳሽ ተሻግሮ የብዙ ቤቶችን በራፍ አልፎ ከወ/ሮ ሙሉ ቤት ደረሰ ። ወ/ሮ ሙሉ ገና ተነስተው በር መክፈታቸው ነበርና ረኸርም ቁመናው ደጃፋቸውን ሞልቶት ሲያዩት ክው ብለው ደነገጡ ። የጠዋት ሰላምታ ሰጥቷቸው ወደ ሥራ ሊሄድ እንደቸኮለና ሊቀመጥም ሊጫወትም እንደማይችል ነግሯቸው እንደ

ቆመ በሰባት ሰዓት ላይ ውዴን ሊወስዳት እንደሚመጣ እንድትጠብቀው ነግሯቸው ወጣ ። ውዴ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ጀምራ ነበር ወ/ሮ ሙሉ ሊሸኙት ሲከተሉት እንደ ወትሮው አልከለከላቸውም ። የጎረቤቶቻቸውን በርካታ ደጃፎች አልፈው የሽንት ቤት ፍሳሽ ቁልቁል የሚወርድበትን ቦይ ተራምደው ገላጣ ቦታ ሲደርሱ ቆም ብሎ የሰባት ሰዓት አመጣጡ ውዴን ከአባቷ ጋር ለማስተዋወቅ ሊወስዳት አስቦ መሆኑን ነገራቸው ወ/ሮ ሙሉ ደነገጡ ወዲያውም ሌላው ቢቀር ከነገር በኋላ አባት ነኝ ብሎ ያለው ሰው እቤት ድረስ መጥቶ ሊተዋወቅ ሲገባው ለምን እሱ ድረስ መሄድ እንዳስፈለገ ቁጣና ቅሬታ በተቀላቀለበት ስሜት ቢጠይቁትም የረባ ምክንያት ሳይሰጣቸው ጥያቄያቸውን ካድበሰበሰው በኋላ ይህንን ፕሮግራሙን ከመምጣቱ በፊት ዝርዝሩን እንዳታውቅ እንዳይነግሯት አሳሰባቸው ። ወ/ሮ ሙሉም ሀሳቡን ተቀብለው እንደ ውዴም የአባትየውን ማንነት ለማወቅና ለማየት ጉጉት እንዳላቸው ገለጹለት ። ይህን ፍላጎታቸውን እንደ ሚፈጽም ተናግሮ እኪሱ ውስጥ ከትቶት በነበረው እጁ ጨብጧቸው ተሰናብቷቸው ሮጠ ። ሊከተሉትም ሊናገሩትም አስበው አልሆነላቸውም ። ፈጥኖ ራቃቸው ። በእጃቸው የያዙትን ገንዘብ ጭብጥ አድርገው ይዘው ምርቃታቸውን ዝቅ ባለ ድምጽ እያነበነቡ ተመልሰው ገቡ ።

አምስት ባለ ጉዳዮች ከጸሐፊው ከአሰለፈች ቢሮ ተቀምጠው ሲጠብቁት ደረሰ ። ቅድሚያ ለማግኘት ሲሉ ከሥራ መጀመሪያ ሰዓት በፊት የደረሱ ነበሩ ። ለሁሉም የጠዋት አጠቃላይ ሰላምታ ሰጥቶ ወደ ቢሮው አለፈ ። በሩን ከፈት አድርጎ ሲገባ የክፍሉ ጠረንና ንጽህና አስደሰተው ። ወትሮ ልብ ብሏት የማያውቀውን ግምትም የማይሰጣት ባለ አረንጓዴ ቀለም የአበባ ማስቀመጫ ጠርሙዝ አበባ

ተደርጐባት አየ ። እሷዋው ያስቀመጠችው ይሆናል ብሎ
ጠረጠረ ። በሙቶ አለቃ አፈወርቅ ቢሮ ከተደረገው እር
ቅና ንግግር ወዲህ ግን አይቷት አያውቅም ። የጽዳት ሠራ
ተኛዋን አስለፈችን ለአጭር ቅጽበት አስታውሷት ወደ
ሌላው የዕለት ሥራው ተመለሰ ።

በጸሐፊዋ በአስለፈች ቢሮ ተራ ይዘው የመጡት
ሁሉ እንዳደራረሳቸው ወደ መኩሪያ ቢሮ እየገቡ ወዲ
ያው ጉዳያቸውን እየጨረሱ ወጡ ። የቀረቡለትን መዛ
ግብት እየመረመረ ተገቢውን ምላሽ ከሰጠበት በኋላ
ጸሐፊውን ጠርቶ ፋይሎቹ ወደ የክፍሉ እንዲመለሱ ነግ
ሯት ቡና እንዲመጣለትም ጠየቃት ። ትኩሱን ቡና እየ
ጠጣ ባገኘው ጥቂት ጊዜ የግል ጉዳዩን ማሰላሰል ጀመረ ።
ሲስተር ፋናዬን ለኑሮ ጓደኝነት የመጠየቁን አስጨናቂ
ውን ነገር እንዴት እንደሚጀመር ፤ የትስ ውይይቱ እን
ደሚደረግ ፤ ከጥያቄው ቀጥሎ የሚመጣው መልስ ቀና
ባይሆን ፤ ለማቃናት ምን ብሎ መንፈሷን ማርካትና ማሳ
መን እንደሚችል የሚኖረውን ችሎታ በመፈተሽ ጭንቅ
እያለ ብዙ ሀሳቦችን እያገላበጠ እያፈራረቀ ተመለከታቸው
የተሻለ ነው ያለው ሀሳብ መጣለትና በእፎይታ ተቀበለው።
አዝማሚያዋን ፤ እውተኛ ውስጣዊ ባህሪዋን ለማወቅ፤
ፍላጐትዋንና ዓላማዋን ለመረዳት ይህ ጥያቄ በቀጥታ ለሷ
ከመድረሱ በፊት ምንተስኖት ብትሰማውና ምክር ቢያ
ደርጉበት መርጦ ይህንኑ በቅርቡ ለማድረግ ወስኖ የተራ
ጊዜ ሰጠው ። የቅድሚያ ሥራው ውዴን ከአባቷ ጋር
ማስተዋወቁ ስለነበር ወደ ውዴና ውብሸት እንዳይላሉ
ጉዳይ ተሻገረ ።

ለምሳ ትንደማይገባ ለእናቱ ከደወለ በኋላ በመሥሪያ
ቤቱ አካባቢ ካለው ምግብ ቤት ቀለል ያለ ምሳ በላ ። የያ
ዛቸው በርካታ ሀሳቦች የመብላት አምሮቱን የጨቆኑበት

በመሆኑ የበላው የረባ ነገር ሳይኖር የጠገበ ሆኖ ተሰምቶ
ታል ። ከምሳው በኋላ ንጹህና በርካታ ሽቀጦች ካለው የፍ
ራፍሬ መደብር ገብቶ ለሕመምተኛ መጠየቂያ ይገባሉ ።
ያላቸውን በቆርቆሮ የታሸጉና ትኩስ ፍራፍሬዎችን ገዝቶ
ውዴን ለመውሰድ ሽቅብ ወደ ስድስት ኪሎ አቅጣጫ
ነዳ ። በተነገራት ሰዓት ከመንደራቸው አካባቢ ሆና ስትጠ
ብቀው ኮሩቅ አይቷት የመኪና ጥሩምባ አሰምቷት ቆመ።
ከታች ከመንደሩ ወደ መኪና መንገዱ እስክትመጣ ድረስ
ልብ ብሎ አስተዋላት ።

ውዴ ወይም ፍሬ መውደድ ከምንጊዜውም ቦማረ
ሁኔታ ለብሳለች ። ይሁም የወ/ሮ ሙሉ ምክርና ትእዛዝ
እንዳለበት አልጠፋውም ። ከበድ ባለው ጭንቅላትዋ ላይ
ችምችም ብሎ የበቀለው ጸጉሯ ብዛቱ ብቻ ሳይሆን ርዝ
መቱም ግርማ ሞገስ ሰጥቷታል ። ሰልከክ ያለው ነጽታዋ
ክሳትና ጉስቁልና በጐዱት ጊዜ የጋረደውን ውበትዋን
ዛሬ ሰውነትዋ መለስ ሲል ይፋ አጋልጦታል ። የቆዳዋ
ቀለም ጥርት ያለ ጠይምነት ይታይበታል ። አነስ አነስ
ያሉት ዓይኖቿ አገላለጣቸው ጨዋነትዋንና ብልህነቷን
ይናገሩላታል ። ከንፈሮችዋ ሳሳ ብለው አውቀው ግጥም
የሚሉ ስለሆኑ ደርበብ ያለ ተፈጥሮ እንዳላት ከሚያሳው
ቁት አካላት መካከል ሌላው ነው ። የአፍላ ወጣትነት
እድሜ ላይ በመሆኗ በጥቂቱ የደረት ልብሷን ገፋ አድርገ
ውት ቢታዩም ጡቶችዋ ትናንሾች ናቸው ። አንጀቷ ከጀ
ርባዋ ጋር የተጣበቀ ሆኖ ለቀቅ ያለ ሽንጥ አላት ። የዳሌዋ
ስፋት ተብሎ የሚደነቅላት ባይሆንም ትክለ ቁመናዋን
ለማሳመር ጥሩ ቅንጅት ፈጥሮ ይታያል ። ወፈር ብሎ ተነ
ስቶ በመጠኑ እስከ ቁርጭምጭሚቷ ድረስ ቀጠን እያለ
ወርዶ የሚያበቃው ባቷ መደላደያው ሎሚ በመሰለ ትንሽ
ተረከዝ ላይ ስለሆነ እሱ ዘንድ እስክትደርስ ድረስ ያለ

CamScanner

ፏትና ያለፈቻቸው መንገደኞች ሁሉ ዝቅ ብለው ሲመለከ
ቱት አይቷል ። እሷም የተጫማችው የባት የተረከዟን
ቁንጅና የሚያረጋግጥ ጥልፍልፍ ነጠላ ጫማ ነበር ።

የመንደሩ ሰው "ወጣት ጡረተኞች" የሚላቸው ሥራ
አጥተው ዋልጌ የሆኑ የሰፈሯ ጐረምሶች ከመንገዱ ጠርዝ
ተኮልኩለው ስላየች እግሮቿ ለመራመድ ሲተሳሰርባት
ልብ ብሏል ። ጐረምሶቹም ጠጠርና የሚደነቁሉ ቃላት
ወርውረውባታል ። ለጉዳት የሚያሳልፋት ዓይነት መተ
ናኮል አለመሆኑን ስላረጋገጠ መኩሪያ ወርዶ ለመከላከል
አልከጀለውም ። ስትደርስ የመኪናውን በር ከፍቶላት
ሰላምታቸውን ከተለዋወጡ በኋላ መንገዳቸውን ወደ ስድ
ስት ኪሎ ሀውልት አቅጣጫ ሆኖ ተንቀሳቀሱ ። ታጥ
ፈው ታቹን ወደ አራት ኪሎ አልፎም ወደ ኢዮቤልዩ
ቤተ መንግሥት ወረዱ ። ከአፍሪካ አንድነት አዳራሽ
ፊት ለፊት ካለው የዛፍ ሥፍራ ሲደርሱ መኪናውን መለስ
አድርጐ ከዛፉ ጥላ ስር አቆማት ። የመኪናውን መቆም
ያዩ ግራና ቀኝ ሕጻናትን በጉናቸው ያንጠለጠሉ እናቶች፥
ዐይነ ስውራን አካለ ስንኩላን ሕጻናትን አስቀድመው መለ
መኛ ያደረጉ አሮጊቶችና ጐልማሶች ፤ አካላቸው በመፈ
ራረስ ላይ ያሉ እየተነፋነፉ የሚያዜሙ ለማኞች ከወዲያ
ከወዲህ እየተሸናከሉ ፤ እየተጓተቱ ፤ እየተማሩ ፤ ከበቧቸው።
በኪሱ ያሉትን ሳንቲሞች ከጨረሰ በኋላ ያልደረሳቸው
የጭቅጭቅ ልመናቸውን ይዘው ደዌ ያበላሸውን አካላ
ቸውን እያሳዩዋቸው ቆሙ ። ቢቸግረው ድምጻቸውን ላለ
መስማት ሰሊ የመኪናውን መስኮት ዘጋው ። ቀነሰ እንጂ
ድምጹ ጭራሹን አልታገደም ነበርና የሚሉት የሚመስ
ሉት ለህሊናው ጭንቀት ፈጥሮበት በዝምታ እያፈራረቀ
አያቸው ። "ከጠፍ መሬት የበቀሉ ከሙጃ የማይሻሉ በወግ
በቅለው በግፍ የሚከስሙ ፍጡራን ከሕይወታቸውና ከም

ታቸው የትኛውን ይደሰቱበት ይሆን ?አለ ለውዴም ሳይ
ሆን ራሱ ለራሱ ያቀረበው ጥያቄ ነበር ። " እየሞቱ ከመኖር
አንድ ጊዜ ሞቶ መገላገል ይሻላል ጋሽ " አለችው ውዴም
በሰዎቹ ሁኔታ ተነክታ ። ለነገሩ ከሷም የጠበቀው መልስ
አልነበረም ። በሰጠችው መልስ ግን ውዴ የአካል ብቻ
ሳይሆን የአእምሮ እድገትም እንዳላት ተረዳበት ።

ብዙ ሳይቆዩ እናቶች ልጆቻቸውን እያንጠለጠሉ፤
እግራቸው በከፊል ያለቀውም እየተሸናከሉ ፤ እውሮቹም
መሪያቸውን ጨምድድው እየተጓተቱ ቁልቁል ወደ እስ
ጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ሲሮጡ ምን እንዳገኙ ምን እንደ
ጠራቸው ለማየት መኩሪያና ውዴም ወደ ቤተክርስቲያኑ
አቅጣጫ አተኮሩ ። አሯሯጣቸው ግን እየተገላመጡ በመ
ሆኑ መለስ ብለው ኮግራ በኩል ላዩን ሲያዩ ከአለባበሱ
ጋር የአካሉ ግርማ ሞገስ ከሩቅ የሚታይ ዩኒፎርም የለበሰ
ቆፍጣና ወታደር ይንጐማለል ነበር ።

መኩሪያም ውዴም ሳይነጋገሩ ጥቂት ጊዜ አለፈ ።
መኩሪያ ጉዳዩን እንዴት እንደሚጀምረው ጭንቅ ብሎት
የመነሻዋን ሀሳብና ቃላት እየመረጠ ነበር ። ውዴ ደግሞ
ጥርሷን ነቅሎ ያሳደጋት ችግር በሰዎች ላይ የሚያደርሰውን
መከራና የበታችነት ፤ የውርደትና የውድቀት ሕይወት
እያሰላሰለች ታዝን ነበር ።

ብልህ ዓይኖቿ አሻግረው የአፍሪካ አንድነት አዳራ
ሽን እየተመለከቱ ኢየሉ ፤ገጽታዋን በከፊል ልብ ብሎ
እያስተዋለ ቆይቶ ፤

" ዛሬ ሰው ለመጠየቅ እንሄዳለን ውድዬ" አላት ።
ትካዜዋን ትታ ሙሉ በሙሉ ፊቷን ወደሱ መልሳ

" ምን ዓይነት ሰው " አለችው

" የታመመ ሰው" ደንገጥ ብላ አፏን እንደመያዝ አለችና

" ጋሽ ውብሸትን ቢሆን ደስ ይለኛል " አለችው።

" አዎ አካሄዳችን ወደሱ ነው"

" አይይ" አለችና ቅሬታ ውርር አደረጋት

" ምነው"

" ፍራፍሬ ሳንገዛ ባዶ እጃችንን እንዴት እንሄዳለን ታዲያ "

" እኔ ገዝቻለሁ "

" ታውቃቸዋለህ እንዴ ጋሽ ውብሸትን " አለችው በመደነቅ ጥያቄ በዚህ ጊዜ በምን አርዕስት እንደሚጀምረው ግራ ገብቶት የነበረውን ጉዳይ መነሻ ጥያቄ ስላቀረበችለት ደስ ብሎት ለጥያቄዋ ረጋ ብሎ መልስ መስጠት ጀመረ ።

" ውድዬ ውብሸትን በሚገባ አውቀዋለሁ ። ከማወቅም አልፎ የተሳሰረ ሕይወት አለን ። የልጅነት የት/ቤት እድሜያችንን ሳንለያይ በሀሳብ በአካል እንደተቀራረብን አልፈነው ሥራ ከያዝንም በኋላ አንድ ቀን ሳንለያይ ጥሩና እውነተኛ ጓደኛሞች እንደሚያደርጉት ሁሉ እያደረግን ኖርን ። በአንድ አጋጣሚ ተቀያየምንና ተለያይተን ቀረን። አሁን ግን ባልጠበቅሁት መንገድ ተገናኘን ። "

" ውይ ጋሽዬ ከጋሽ ውብሸት ጋር የነበራችሁን መተዋወቅና ለምን እንደ ተጣላችሁ ዝርዝር አድርገህ ንገረኝ እኔ እኮ እነ ሲስተር ቤት ታመሙ የተባለ ቀን እንደነገርኳችሁ ከዓመት በላይ እሳቸው ቤት ሠርቻለሁ ።" አለችው ለመስማትና ለማወቅ ያላትን ጉጉት በሚያሳይ ስሜትዋ

ትኩሻውን ያዝ አድርጋው በሚያባብሉ ዐይኖችዋ እያየችው ።

" እሱን እሺ ። ከዚያም በኋላ የምገልጽልሽን ታሪክ ሁሉ ልብ ብለሽ አድምጪኝ ። "

" እሺ" አለችው በጉጉት

" በደብረ ብርሃን ከተማ በኃ/ማርያም ማሞ ት/ቤት የአስራ ሁለተኛን ክፍል ፈተና አልፎ ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት አዲስ አበባ ሲመጣ እኔም ከምኒሊክ ት/ ቤት አስራ ሁለተኛን አልፌ ነበርና በዩኒቨርስቲ ግቢ ተገናኘን አንድ መኝታ ክፍል ለሁለት ደረስን ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ተጣላን ድረስ የሚያስቀና የጠበቀ ጓደኝነት ነበረን ። " ጥቂት ዝም ብሎ አንገቱን ደፋ አደረገ ።

" ታዲያ ምን አጣላችሁ "

" የተጣላነውማ በአንድ ነገር ላይ የተለያየ አቋም መያዛችን ነበር ። እንዲህ ነበር ውድዬ ሥራ ይዘን ወደ ክ/ ሀገር ስንሄድ እንደ አጋጣሚ ምድባችን የተለያየ ነበር ። ሆኖም እጅግ የተራራቀ ስፍራ ስላልነበር በወር ውስጥ ሁለቴ ቢያንስ አንድ ጊዜ እንተያያለን ። በዚህ መካከል አንዲት ሴት ጓደኛ ተዋውቆ ነበር ። ጓደኛው እንደሆነች ካስተዋወቀኝ በኋላ ሴትዮዋ በነበራት ጸባይና ጥሩ ሰውነት የማከብራት እንደ ጓደኛዬ እንደ ውብሸት የማያት ነበረች። ከብዙ ቆይታቸው በኋላ በመጽነስዋ ምክንያት ይጣላሉ ። ጥላቻውን ለማርገብ በመሀል ገብቼ ነበር ። ልፈታው አልቻልኩም ። ውብሸትም ምክሬን ሊቀበለው አልፈለገም። የተጸነሰችው ልጅ ተወለደች። የተወለደችውንም ህጻን ሊረዳና ሊቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ በዚሁ ሳቢያ ብዙ ተጨቃጭቀን በወሰደው ግትር አቋም ተቀይሜ ተጣላሁት ። "

" ግፈኛ ናቸው " አለችው በመሀል አቋርጣ ።

“ እሱ እንኳን ያለ መብሰልና ጉርምስና ነበር” አላት ትዝብትዋን ለማለዘብ አስቦ ።

“ በዚያ ደረጃ ለተማረ ሰው ይኽንን ማመዛዘን የሚያቅተው አይመስለኝም ። በሰው ላይ ለመጨከን አስበው ያደረጉት ካልሆነ በቀር ።”

“ በመሠረቱ ውብሽት አስተዋይና ደግ ሰው ነው ። ያ ጊዜ የአፍላ ወጣትነት ጊዜ በመሆኑ ጉዳዩን በወጉ አላስተዋለውም ነበር ለማለት እደፍራለሁ ።”

“ ቢሆንም ሰው ለወለደው ልጅ ከጨከነ ለማን ቀና ይሆናል ። አንተስ የተገነዘብከውን እንዴት እሳቸው ሳይረዱት ቀሩ ። ለማንኛውም ያች ልጅ የት ደረሰች ።”

መኩሪያ እያሳሳቀ ያለ መብሰል ነው ፤ ወጣትነት ነው ፤ እያለ ሊያቃልለው ቢሞክርም ኀዘን እያለች የሰጠችው ትችት ወገቡን ቆርጦታል ።

“ ልጅቷማ ታማሚ ሆና በሥቃይ ብታድግም አትሙች ብሎ የፈጠራት እድለኛ ልጅም ስለሆነች በእናቷ ጥረት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ ደርሳለች ።”

“ በዚህም ደረጃ ላይ እያለች አባትና ልጅ አይተዋወቁም” ?

“ እስከዛሬ አለመተዋወቃቸውን አውቃለሁ ። ልጅቷ ግን የማወቅ ፍላጎት እንዳላት እሰማለሁ ። ተገቢውን የአባትነት ፍቅር እርዳታና እንክብካቤ የነፈጋትን ሰው በአባትነት አልጠራውም አላስተዋውቃትም ብላ እናቷ ቆርጣ እንደ ነበርና አሁን ግን ሀሳብዋን በመለወጥ ላይ መሆኗን ሰምቼአለሁ ። ” አላት ስሜትዋን ለማንበብ አይኖቹን በፊቷ ላይ ተክሎ ።

“ ሌላው ቢቀር የሰውየውን መልኩን ጠቅላላ ቁመናውን ማየት ራሱ ለልጅቷ የተለየ ስሜት ሊሰጣት ይችላል እንደኔ አንገል ሕልም አታልምም ። በሠራው ሥራ ግን እንደ ልጅቷ ውሣኔ ሊሆን ይችላል መቅረብ ወይም መራቅ ይቻላል ። እናትዬዋም እንዲያውም ልትኮራና የጥረትዋ ውጤት የሆነችውን ልጅዋን እስዋው እራስዋ ይዛ ከሰውዬው ዘንድ በመሄድ የጣላት ሕጻን የደረሰችበትን ደረጃ ነግራ ፤ በፊትም እንዳልረዳት ሁሉ አሁንም ከሱ እርዳታ እንደማትሻ እየኮራች አስረድታ ነገር ግን የትውልድ መሠረትዋን ማየት ስላለባት ብቻ ልታስተዋውቃቸው እንደመጣች ገልጻ ማስተዋወቅ ነበረባት ።” አለችው የሰዎቹ ሁኔታ በምናብዋ እየታያት ቁጭት በተጫነው አባባል ።

“ ሰዎች በኑሮ ውስጥ መጋጨታቸው ያለ ነው ። እንደመጣላትም መታረቅም ይኖራል ። ዋናው ቁም ነገር አባትም ሆነ ልጁ አንዱ ሌላውን እንደሚናፍቁ የታወቀ በመሆኑ መተዋወቃቸው አስፈላጊ ነው ። አይመስልሽም ውድዬ ” አላት በድጋሚ ።

“እኔም ብያለሁ እኮ ጋሽዬ ፣ የሁለቱ የአባትና የእናት መቀያየም ራሱን የቻለ ጉዳይ ነው ። በዚያ ጥል ምክንያት በደል ደርሶባት ከሆነ ልጅቷ ነፍስ ካወቀች ጀምሮ የተገነዘበችው ብዙ ነገር ስለሚኖር የራሷ የሆነ ውሳኔ ለመውሰድ አትቸገርም ። ነገር ግን አባትዋን የማወቅ መብቷ መጠበቅ አለበት ። ለማንኛውም ለኔ ግን እኮ በጣም ደግ ነበሩ ። የደብተር መግዣ እያሉ ከደመወዜ ውጭ ብዙ ጊዜ የሰጡኝ ገንዘብ ትዝ ይለኛል ። በዚህ ሥራቸው ግን እኔ እንጃ ታዘብኳቸው ” አለችና ያኔ ያየችውን የህሊና መሸሻንና የታየች አባ ጨፍቅን ታሪክ አስታውሳ አዳምራ አሰላሰለችው ። በመቀጠል

" ለማንኛውም ለኔ በዋሉልኝ ውለታ ምክንያት ብጠይቃቸው ደስ ይለኛል ። " አለችው ።

" ውድዬ አንድ እንድትገነዘቢልኝ የምፈልገው ነገር አለ ። አንድ አጋጣሚ ይፈጠርና በሰው ላይ ችግር መከራ ጥሎ እስከመጨረሻው የማይረሳ ጥቃት ቢያደርስ ያሳዝናል ያስቆጫል ። ይኸ ግን ለየት ያለና ብርታት ውጤት የታየበት በመሆኑ ጥፋቶችን ሁሉ ሳናከብድ ተደስተን ልንቀበለው የሚገባ ነው ። ይህ የገለጽኩልሽ ታሪክ ሁሉ በኛው አካባቢ የሚሽከረከር ነው ። ውብሸት ጓደኛዬ ነው ። ምንቴም እህቴ ናት ላንቺ ግን ውብሸት አባትሽ ነው ። ምንቴ ደግሞ ወላጅ እናትሽ ናት ። ወ/ሮ ሙሉ ፤ አያትሽ የምንቴ እናት ናቸው ። ይህ ምስጢር ከዚህ በኋላ ተገልጦልሽ ትክክለኛውን የራስሽንና የወላጆችሽን ገጽታ መመልከት አለብሽ ። "

ንግግሩን ሳይጨርስ ከአንገቱ ላይ ተጠምጥማ ድንጋጤ ሰበቃት ። ቀስ በቀስ ማልቀስ ጀመረች የድንጋጤ የጭንቀት ስሜትዋን በልቅሶ እንድ ትወጣው ትከሻዋን እየደባበሰ እድል ሰጣት ። ዓይኖችዋን ጠራርጋ ቀና ካለች በኋላ አጐንብሳ ጣትዋን እያፍተለተለች ዝም አለች ። መኩሪያም ዝም ብሎ ተመለከታት ። የምትናገረው የምትጠይቀው ብዙ ሀሳብ እንደሚኖራትና ለጊዜው ግን ድንግርግር ብሎዋት ቃል መተንፈስ እንዳቃታት ባየ ጊዜ ወደ ማበረታታቱ ገባ ። ግራ ግብት ብሏት " እንዴት ሊሆን ይችላል " ከማለት በቀር አፍታትታ ሀሳብዋን መናገር አቃታት ።

" ምንቴ ምን ሆና በሽተኛ ሆነች ታዲያ " አለችው የሙት ሙትዋን ቆይታ

" እሷማ አንቺ ከተወለድሽ በኋላ ታማሚ ሆነሽ ውብሸት ሊረዳሽ ፈቃደኛ አልሆንም ባላት ወቅት በብስ

ጭት ብዛት ታማ የአእምሮ መታወክ ደረሰባት ፤ ከልጅነትሽ ጀምሮ ከወ/ሮ ሙሉ ጋር የኖርሽና ያደግሽ ስለሆነ ሀሊናሽ እንዳይረብሽ ሲባል ትክክለኛው ሁኔታ እስከዛሬ አልተነገረሽም ። ምንቴም በእግዚአብሔር ቸርነት ከብዙ ዓመት ሕመም በኋላ ዳነች ። አንቺም በአካል አድገሽ በአእምሮ በሶለሽ ፤ በውበት ቆንጅተሽ ለዚህ ደረስሽልን ።" አላት ።

መንፈስዋ እየሰከነ መምጣት በመጀመሩ በአነጋገሩ እንደ መሳቅ ብላ

" እኔ ግን " አለችና ዝም አለች

" ምንድነው ውድዬ የምትፈልጊውን ሁሉ ተናገሪ የሚሰማሽን አትደብቂኝ የበፊቱም የወደፊቱም እኔነቴ ላንቺ አይለወጥም " ጭንቅላትዋን በሰፊው መደፉ ከትከሻው ላይ ዘንበል አድርጐ ደባበሳት ።

" እኔ ግን ያንተን አጐትነት የእማዬን እናትነት እንዳመንኩበት ብቀር እወድ ነበር "

" ያ ሁኔታ ምንም ኃይል ሳይለውጠው ይኖራል ። አሁን የነገርኩሽ ታሪክ ሁሉ አንድ የተሟላ ሰው ማወቅ የሚገባውን የዘር የትውልድ መሠረቱን ማወቅ እንዳለበት ሁሉ እንድታውቂ በማለት የነገርኩሽ ነው ። ካወቅሽው በኋላ የቀረው ግምትና ውሣኔ ሁሉ ያንች ነው ። መኩሪያ አጐትሽ ነው በፊትም ወደፊትም እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ።" አላትና ግንባሯን ሳማት ። እሷም በስስት ስሜት አንገቱን እቅፍ አድርጋ ትከሻው ላይ አዘነበለች ።

" እንግዲህ አንቺም ቢሆን የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆነሻልና አስተካክይኝ ፤ አንድ ሊቅ ስሙን ረሳሁት ፤ . . . ዓለም የተውኔት መድረክ ናት ልብ የሚለው ቢኖር እያንዳንዱ ሰው ተዋናይ ነው ።" ብሏል እና እኛም በቤተሰ

ባችን መካከል የተጀመረው ተውኔት አጨራረሱ በደስታ እንዲሆን በተለይ እኔና አንቺ ጥሩ ሚና መጫወት አለብን ። ”

“ እሺ እንዴት እናድርግ ”

“ ዛሬ አንቺን ከውብሸትና ከወንድሞቹ ጋር እንድ ትተዋወቂ አደርጋለሁ ። ነገሩ አውቆ መተዋወቅ ነው ። ከዚያ በኋላ ውብሸትና እማማ ሙሉ እንዲተዋወቁ ይሆ ናል ። ቀጥሎም ምንቴ ሁሉንም ለእግዜር ይቅር ብላ እን ድትጠይቀው ግትር የጥላቻ የቂም አቋሟን እንድትለውጥ እናደርጋለን ።”

“ መተዋወቁ ከሆስፒታል ከወጡ . . . ከወጣ . . . በኋላ ቢሆን አይሻልም ”

“ አባትሽ ስለሆነ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ አንተ ልት ይው ይገባል ” አላት የተጨነቀችበትን አባባል ወስና ቀጠል አድርጎም ። “ ውብሸት የታመመው ባላሰበውና ባልጠበቀው ሁኔታ ከምንተስኖት ጋር ጎረቤት በመሆኑ ከዚያም በላይ በአንድ የአካባቢ ኮሚቴ እንዲሠሩ በመመ ረጣቸው ብቻ ሳይሆን አንቺ የሷ ልጅ ሆነሽ በመገኘትሽም ጭምር ነው ። ይህ ሕመሙ ምናልባት ረጅም ጊዜ ሊወስ ድበት ይችል ይሆናል ። ለማንኛውም ከዚህ በኋላ ነገር ለመሸፈን እድል አንሰጥም ። ”

“ ሚስቱስ ”

“ ቅር ሊላት ይችላል ። ሆኖም እውነትን መጋረድ እንጂ ማጥፋት አይቻልም ስለዚህ ዛሬም ባይሆን ወደፊት እንድታውቀው ይደረጋል ።”

“ዛሬ ገብተን ጠይቀን ብቻ እንወጣለን ማለት ነው ”

“ እሱማ ውብሸት ልጁ እንደሆንሽ አውቋል ። አባ ትነቱን አንቺ ብቻ ነበርሽ ያላወቅሽውና ካወቅሽ በኋላ በሰው መሀል የምንናገረው አይኖርም ጠይቀነው አይተ ነው እንወጣለን ። ”

“ በሽታው ግን ምን ያህል የፀና ቢሆን ነው ለመዳን ረዥም ጊዜ የሚወስድባቸው . . የሚወስድበት ”

“ የደም ብዛት ወይም የደም ግፊት ሕመም ስለነበ ረበት በድንጋጤ የተነሣ ከመኖፎ ደረጃ ላይ ለ ያደርሰው ነበር ቶሎ የሐኪም እርዳታ በማግኘቱ ተርፏል ። አሁን እጅግ እየተሻለው ነው ። ”

“ ጥሩ እንግዲህ አድርጊ የምትለኝ ሁሉ አደርጋለሁ። ምንቴን ግን አንተው አናግራት ። ” አለችው መደነቅና መደንገጥ ትንደወረራት ።

ሰዓቱን አየት አድርጎ የመግቢያው ጊዜ በመድ ረሱ መኪናውን አንቀሳቀሰ ። አልፎ አልፎ መለስ ብሎ እያያት ፈገግታው ግራ ቀኝ ጉንጮቹን ስርጉድ እያደረ ጋቸው የፍልውሀን መስመር ይዘው ወረዱ ። ውዴም “ ውይ ጉድ ” እያለች እየተገረመች ከጊዜ ወደ ጊዜ ፊቷ ላይ የፈገግታ ፀዳል ትየበራ ከዘውዲቱ ሆስፒታል ፊት ለፊት መኪናው ጥግ ይዞ ቆመና ወረዱ ። ሕሙማን ጠያቂዎች ከበሩ ላይ ተሰብስበዋል ። የተጠቀለለ ነገር በደረቱ አስጠግቶ ያላቀፈ በዘንቢል በከረጢት በላስቲክ ምናምን ያላንጠለጠለ የለም ። መንገዱን ሳየቋርጡ ቆመው በሩ ላይ የሚራኮቱትን ሰው በዝምታ ተመለከቱ ። መኩ ሪያ አልፎ አልፎ ዓይኖቹን ወደ ፎቁ ይወረውራል ። በሰ ዎቹ መካከል ደምቃ የምትታየው ሴት ዞር ስትል “ውይ” ብላ ውዴ አፏን ያዘች ። ታየች አባ ጨፍቅ እንደ ተሾመ ደው ሽቅርቅር ብላ ተውባ የወርቅ እንክብሎችዋን በአን ገትዋ በጆሮዋ በጣቶችዋ ተሸክማ ነበር ። መገረምዋን

ተመልክቶ ምን እንደሆነች ቢጠይቃትም ለመኩሪያ ስለ ታየች አባ ጨፍቅ ማንነት መናገር አልፈለገችም ነበርና "ምንም አይደል" ብላ መለሰችለት ።

የግቢው በር ተከፍቶ ጠያቂዎች ሁሉ ተሻሮጉደጉ ደው ከገቡ በኋላ መኪናው ውስጥ ያኖረውን መጠየቂያ ፍራፍሬ ይዘው ወደ ሆስፒታሉ ግቢ ደረሱ ። ከሁለተኛው ፎቅ ላይ መስኮት ከፍታ ቁልቁል ታያቸው ነበርና ቀና ሲል ከሲስተር ጋር ዓይን ላይን ተጋጩ ። የቀኝ እጅ አውራ ጣቱን በማሳየት ያሰበውን ከፍጻሜ እንዳደረሰ አሳወቃት። ሲስተር ፋናዬ ክፍቱ መውጫ ደረጃው ላይ ቆማ ጠበቀ ቻቸው ። የሆነ ነገር በጆሮዋ ሹክ ብላ ካሳቀቻት በኋላ ውዴን ስማ መኩሪያን ጨብጣ እሷ ፊት ፊት እነሱ ተከ ትለው ወደ ቁጥር 205 ክፍል አመሩ ። ብዙ ጠያቂዎች ነበሩ ። የአበባየሁ ዘመዶች ቅላታቸውን ጥቁር ልብሳቸው እያጉላው ካለው ሁሉ ተለይተው ይታወቃሉ ። ከክፍሉ ተርፈው በኮሪደሩ ላይ ቆመዋል ።

ፈንጠር ብለው ቆመው ያወሩ የነበሩት ሣህለ ድን ግልና ታደሰ እንዳይላሉ የነመኩሪያን መምጣት ከርቀት ሲያዩ ወሬያቸውን ትተው ይመለከቷቸው ነበር ። የአብ ዛኛው ሰው ዓይን ያረፈው ግን ከውዴ ላይ ነበር ። ውዴም በሰማችው ዱብ ዕዳ ታሪክ ስለተረበሸች ከበርካታ ሰዎች መካከል የመገኘትና የመካፈል ልምዱም ውሱን በመሆኑ፤ በተለይም ገና የምትተዋወቃቸው የአባቷ ወንድሞች በአ ካባቢ ትንዳሉ በማወቋ እፍርና ጭንቅ ማለቷ ገሀድ ይታ ይባታል ። የውብሽት ጠያቂ ዎች በተለያየ አቅጣጫ የመ ጡና የበረከቱ ስለ ነበሩ ገብቶ ለመጠየቅ ተራ መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሰው ይህንኑ በመገንዘብ ተራ በተራ እየገባ ይጠይቀዋል።ታየች አባጨፍቅም ገብታ ለመጠየቅ እድልና ተራ ትስክታገኝ ድረስ በኮሪደሩ ላይ ቆማ ካሉት ሁሉ ደም

ታ ትታያለች ። መኩሪያና ውዴ ብቅ ባሉበት ወቅት የነበራት አስተያየት ለትዝብት ዳርጓታል ። የውዴ መም ጣት ከሰማይ የመውረድ ያህል ሆኖ ተሰምቷታል ። የነበራትን እቅድና ምኞት በእንጭጩ ቀጭታው አድራ ሻዋን ሰውራ የተለየቻት አድርጋ ትታስባት ኖራ ነበርና በዚህ እድገትና ወበት ተለውጣ ስታያት በይሉኝታ ራስ ዋን ገትታ መቆጣጠር ተሳናት ። ጥግ ጥጉን ይዘው ከቆ ሙት ሰዎች መካከል ወደፊት ራመድ ብላ በፈገግታ እየ ፈካች ወጥታ ውዴን ጠርታ አገላብጣ ሳመቻት ። ደግማ ደጋግማ እስከዚያ ቀን የት እንደ ነበረች ጠየቀቻት ። ከላይ እስከ ታች በመደነቅ እያየቻት የልቧን ሳታነጋግራት በትህትና ይቅርታ ጠይቃት መኩሪያ ውዴን ከታየች ነጥሎ ወሰዳት ። ውዴ እንደ እፎይታ ትትቆጥረው ታየች አባ ጨፍቅን ግን ብስጭት አደረጋት ።

ውዴ ከታየች ጋር ስላምታ እስክትለዋወጥ ድረስ ከሣህለ ድንግልና ከታደሰ ጋር ተነጋግሮ ቀደም ሲል የሳ ወቃቸውን የታሪክ ባለቤት ይዟት እንደ መጣ አስታውቆ ነበርና ፤

"ፍሬ መውደድ" አለና አስተዋወቃት ። የመ ደነቅ የመደንገጥ ሁኔታ እየታየባቸው ሣህለ ድንግልና ታደሰ እንዳይላሉ ተቀባብለው ሳሟት ። ከዚያ ወዲያ ሰው ጋብ ብሎ መግባት እስኪችሉ ድረስ እስዋን ከመካ ከል አድርገው በፍቅርና በዝምድና አመለካከት እያዩዋት አጨዋወቱዋት ። ውዴ ግን ለጠየቋት ሁሉ መልስ ከመ ስጠት በቀር አንዳችም ከራስዋ አቅንታ የሰነዘረችው ጥያ ቄና ሀሳብ አልነበራትም ። የዘመናት ድርጊትና ሁኔታዎች በዓይነ ህሊናዋ ሥር ተሰልፈው እያለፉ ትመለከት ነበር ። ወንድማቸው ለ1ኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርት የደረ ሰች ልጅ እንዳለችው አንዳች ጭምጭምታ እንኳ ሳይ

CamScanner

ሰሙ በመኖራቸው እያዘኑም እየተገረሙም የውብሸት
ወንድሞች ዐይኖቻቸውን ከውዴ ላይ ሊያነሱ አቃታቸ
ቸው ። ማንም የውጭ ተመልካች ውዴንና አጐቶችዋን
በአንድነት ሲያይ ያላቸውን የሥጋ የደም አንድነት ባይ
ነግሩትም ከቁመናቸው ከኢጽታቸው ከዐይነ ውሀቸው
ሊረዳ አላዳገተውም ። አካልዋ ሥጋ ከደረበ ወዲህ ፤የተ
ሚሉ የሴት ቁመናና ቅርጽ ካሳየች ወዲህ መልኳ ተስተካ
ክሎ የውብሸትን ገጽታ መስሏል ። ታየች አባ ጨፍቅም
ምናልባት ይኸው መመሳሰል ሳይሆን አይቀርም አትኩራ
አንድ ታይና እንድታጣራ ያስገደዳት ።

ክፍሉን ሞልተውት የነበሩት የአበባየሁ ቤተሰቦች
ሲወጡ ፤ ማህለ ድንግልና ታደሰ ቀድመው መኩሪያና
ውዴ ተከትለው ገቡ ። ሲስተር ፋናዬም በትንሽ ዕቃ ላይ
መድኃኒት ይዛ ገባች ።

የጤናውን ሁኔታ አዳሩንና ውሎውን ወንድሞቹ እየተቀ
ባበሉ ሲጠይቁት ቆይተው ቀና ሲሉ መኩሪያና ውዴ
ከፊቱ መቆማቸውን ሲያይ ክንዱን ከዐይኖቹ ላይ ጭኖ
ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ ። ወዲያው ክንዱን አልፎ እንባ
ው ሲፈስ መኩሪያ መሀረሙን አውጥቶ ከፊቱ ላይ የፈሰ
ሰውን እንባ ጠርጐ ግንባሩን ስሞ የማጽናኛና የግሣጼ
ቃል ተናገረው ። ውብሸት የሰጠው መልስ አልነበረም።
ወዲያው መኩሪያ ውዴን ሳብ አድርጐ ወደ ውብሸት አቀ
ረባት ። ውብሸት በቀኝ እጁ እጅዋን ይዞ እያያት አለቀሰ ።
ሁሉም አለቀሱ ። ጐንበስ ብላ እንድትስመው ጐተት ሲያደ
ርጋት እንባ ያረጠበውን ገጽታውን በሚንቀጠቀጡ ከናፍሯ
ሳመቻቸው ። በመጨረሻም ከአልጋው አጠገብ ሸብረክ
እንደ ማለት አሉችና ጭንቅላትዋን ከአልጋው ጠርዝ ላይ
ደገፍ ስታደርገው ራሱን ከራስዋ ላይ አስደግፎ እንደገና
እንባውን አፈሰሰ ። በአካባቢው የቆሙት ሁሉ ልባቸው

በሀዘን ተሰበረ ። ወንድሞቹም ሆኑ መኩሪያ እንባቸውን
ማገድ አቃታቸው ። መናገር እየፈለገ አፉን እያንቀሳቀሰ
ባለ መቻሉ እየተወው ወዲያው ያነባ ነበርና ውዴን
ካገኀበሰች በት አስነስቶ ፊቷን ጠራርጐ የውብሸትን
ፊት እንዲሁ እንባውን አብሶ ሁሉም ቢሆኑ ሊደሰቱ
ለእግዜር ምስጋና ሊያቀርቡ እንደሚገባቸው አሳስቦ መኩ
ሪያ የነበረውን ሁኔታ ለመለወጥ ሞከረ ።

ውዴ በወቅቱ የአንደኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትም
ህርት በመከታተል ላይ እንደ ሆነች ኮራ ብሎ ከተናገረ
በኋላ ስላለፈው ሳይሆን ስለ ወደፊቱ ግንኙነትና መተሳ
ሰብ ጥሩ ሥርዓትና እቅድ መኖር እንዳለበት ከማህለ
ድንግል ጋር ጐላ አድርገው በሚነጋገሩት ጭውውት ላይ
መኩሪያ ጠበቅ አድርጐ አሳሰበ ። ወዲያው ውብሸት እዚህ
ደረጃ በመድረሷ ለማድነቅ እጇን ደረጋላትና ሄዳ ጨበጠ
ችው ። መኩሪያንም በምልክት ጠርቶት ከአጠገቡ ሲቀ
ርብ ጭንቅላቱን ወደ ታች ዝቅ አድርጐ አቀፈው ። ለውዴ
ከዚህ ደረጃ መድረስ ዋናው ምክንየት መኩሪያ እንደሆነ
በመገመት ምስጋና ለማቅረብ ያደረገው ሙከራ ነበር ።
መኩሪያም በተኛበት የውብሸትን ሽበት የወረረውን
ጭንቅላቱን እየደባበሰ ከራስጌው ቆመ ።

ባለቤቱ አበባየሁ ተመልሳ ስትገባ ከሲስተር ፋናዬ
በቀር የሁሉም ዐይኖች በእንባ ቀልተውና ረጥበው በሁ
ሉም ገጽታ ላይ ሀዘን ተቀርጾ በማየቷ ደነገጠች ። ወንድ
ሞቹን ምን አዲስ ሁኔታ እንደ ተፈጠረ ብትጠይቅም
ከ'ምንም የለም' ሌላ መልስ ስላጣች ውብሸትን ግንባሯን
ቋጠር አድርጋ ጭንቅላቷን በማወዛወዝ በምልክት በቃ
ልም ጠየቀችው ። መጻፊያ እንድትሰጠው በምልክት
ነገራት ። ትንሽ ወረቀትና እስክሪፕቶ አቀበለችው ።የሚ
ንቀሳቀሰውን ቀኝ እግሩን ወደ ላይ አጥፎ ወረቀቱን አስ

CamScanner

ደግፎ አጭር ቃላት ጽፎ ሰጣት ። ካነበበች በኋላ ዐይኖቿ ያረፉት በቀጥታ ውዴ ላይ ነበር ። ውዴ ግን አንገቷን ደፍታ ወለሉን ታይ ነበር ። መኩሪያ በአበባየሁ ትከሻ ላይ አንጋጦ የጻፈላትን አነበበው ። " ልጄ ናትና እወቂያት" የሚል ነበር ። አበባየሁ ቀይ ፊትዋ ወዲያው ሲቀየር ታየ። የውብሸትን ወንድሞችና መኩሪያን ተራ በተራ በግልምጫ አስተያየት ከአየቻቸው በኋላ ፤ " ለውርስ ክፍየ የተሰናዳችሁ ይመስላል ። " አለች ከአልጋው ወደ መስኮቱ እየተራመደች ። ማንም መልስ አልሰጣትም ። መረስ ብላ ወደ ውዴ እየተመለከተች ፤ " የኔ እህት ሲሞት መጥተሽ ንብረት ትተሳሰቢ.የለሽ ላሁኑ ከዚህ ክፍል ውጪ" አለቻት በጩኸትና በጥላቻ ። ማንም ከቆመበት አልተንቀሳቀሰም ። እንድታየው ፈልጎ ውብሸት ምልክት ቢሰጣትም መልስ ልትሰጠው ፈቃደኛ ስላልነበረች የያዘውን እስክሪፕቶ ወርውሮ ከደረቷ ላይ አሳረፈው ። ቀጣ ፍፈጠጣቸው ዐይኖቿ ሰትመለከተው እንድትወጣ ምልክት ሰጣት ። አበባየሁም የራስህ ጉዳይ በሚል አስተያየት ገላምጣው ትታው ወጣች ። ሁሉም በነበሩበት በዝምታ ቆመው ቀሩ ። ከአልጋው ግርጌ ቆማ ሁኔታውን በጥንቃቄ ስትመለከት የነበረችው ሲስተር ፋናዬ ወደ ፊት ራመድ ብላ " ገና ዛሬ ለእውነት በእውነት መቆምህ ሊያስደስትህ ይገባል " ብላው እሷም ወጣች ። ማን እንደሆነችና ስለማን እንደምትናገር ግር ያላቸው ሣህለ ድንግል ፤ ታደሰና ውብሸት ጦቻ ነበሩ ። መኩሪያ ፤ ማንነቷን ከገለጸላቸው በኋላ አቅሚ በፈቀደው ሁሉ ለውብሸት ጤንነት መደረግ ያለበትን እርዳታ እንዲያገኝ መድከሚ ያለ ምክንያት እንዳልነበረ ገለጸው ።

ውብሸት ቀኝ እጁንና እግሩን እያንቀሳቀሰ በብስጭት በሀዘን ተቅበጠበጠ ። ከራስጌው ወደ ቆመው መኩሪያ

አንጋጦ ተመለከተና መጻፊያ እንዲሰጠው ጠየቀው ። ወረቀትና እስክሪፕቶ አቀረበለት ። ወዲያው ጽፎ ለመኩሪያ አቀበለው ። መኩሪያ በቃሉ "አዎ" አለው ፈገግታ በገጽታው እያንሠራራ እንደገናም ጽፎ አሳየው ። "ችሺ" አለው ። ቀጥሎም በወረቀቱ ጀርባ ላይ ጽፎ ለውዴ ዘረጋላት ። ተቀብላ አነበበችው ። እሷም "አዎ" አለችው መናገር እንጂ መስማት እንዳልተሳነው ተረድታ ነበርና ። ውብሸት ጽፎ የጠየቀው መኩሪያ ከልቡ ይቅር ብሎት እንደ ሆነና ሊያስታምመው ፈቃደኛ እንደሆነ የዚያን እለቱን አዳር አብሮት እንዲያድር የሚጠይቅ ነበር ። ውዴንም የጠየቃት ሙሉ ይቅርታ እንድታደርግለትና ልመናውን እንድትቀበለው የሚማጸን ነበር ።

መኩሪያና ውዴ ለመውጣት ሲዘጋጁ ታየች አባ ጨፍቅ በሩን ከፍታ ገባች ። ቢደነግጥም ግንባሩን ሰብሰብ አድርጐ ቆፍጠን ብሎ ውብሸት ተመለከታት ። " እግዚአብሔር ይማርህ አቶ ውብሸት " በማለት የለበጣ ፈገግታዋን አሳየችው ። ሰላምታዋን በጭንቅላቱ እንቅስቃሴ መቀበሉን አሳየት ። የውዴን ሁኔታ ተመልክቶ መኩሪያ ፈጥኖ ይዟት ወጣ ። እንደሚመለስ ግን ተናግሮ ነበር ።

ከቢሮዋ ሲደርሱ ሲስተር ፋናዬ አልነበረችም ። ከቢሮዋ ገብተው የነበሩበትን ሁኔታና ስሜት እያወሱ እየተጫዋወቱ ጠበቋት ። እሷም ለብቻዋ ነገር ስታሰላስል ቆይታ ነበርና ስታያቸው ያስቆጣትንም ያስገረማትንም ጉዳይ ልታካፍላቸው ፈልጋ የተሰማትን ሁሉ አወራችላቸው ። መኩሪያ ለአዳር እንደሚመለስ እና የሲስተር አዳሪ መሆን ደግሞ የበለጠ እንዳስደሰተው የተረፈውን ሁሉ እንደሚጨዋወቱ ገልጾ በቀጠሮ ለጥቂት ሰዓታት ተለያት ። መኩሪያና ውዴ ለአፍንጮ በር መንገድ ተነሱ።

ከሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ ከመንገዱ ማዶ ወደ ቆመችው መኪና ሲሄዱ ውዴ ገና በሰማችውና ባየችው ሁኔታ ትደነቅ ነበር ። መኪናው ዘንድ ደርሰው ከመግባቷ በፊት ወደ ኋላ እንደ ድንገት ዞር አለች ። ከርቀት በፈገግታ የሚ መለከታት ሰው አየችና የመኪናውን በር በዝግታ መለስ አድርጋ ተመልሳ መንገዱን ተሻግራ ሄደች ። መኩሪያም ከተቀመጠበት ተነስቶ መኪናውን ተደግፎ ቆሞ ተመለከታት ። ከምትስማት ሴት ጋር ተነፋፍቀው የተገናኙ ይመስላሉ ። መሳሳማቸው የለበጣ ዓይነት አልነበረም ። እርጋታዋና ውብትዋ ያለ ምንም ለውጥ አብሯት እንዳለ ውዴ ልብ ብላ አስተዋለች ። ህሊና መሸሻ የውብሸት እንዳይላሉን መታመም ሰምታ ልትጠይቀው እንደ መጣች ለውዴ ነገረቻት ። ውዴም ጠይቃው መመለስዋን አስረ ድታት ለሌላ ጥያቄ እድል ሳትሰጣት ሰው እንደሚጠብቃት ገልጻ በትህትና ተሰናብታት ተመልሳ ተሻግራ ወደ መኩሪያ ሮጠች ።

በቅርብ የምታውቃትና የምትወዳት ሴት መሆኗን እንጂ እንዴት እንደ ምታውቃትና ማንነትዋን አልነገረችውም ። መንገዳቸውን በቸርችል ጐዳና አቅንተው በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በኩል አድርገው ወደ አፍንጮ በር ገሰገሱ ። በጉዞአቸው ላይ ባደረጉት ውይይት ወ/ሮ ሙሉም ግልጹን ሁኔታ በዚያው ዕለት ሰምተውት በነጋታው እሁድ ሄደው እንዲጠይቁት ተስማምተው ወሰኑ። አፍንጮ በር ዳገቱ ላይ በቀኝ ጠርዝ በኩል መኪናውን ወደ መንደሩ መግቢያ አስጠግቶ ካቆመ በኋላ ሁለቱም ተያይዘው ወደ ነውዴ ቤት ወረዱ ። መንገዱ ዳር ተኮልኩለው አልፎ አልፎ ብቸኛ ወጣት ሴቶችን ሲተናኮሉ የነበሩት ጐረምሶች አልተነሱም ። ከመኩሪያ ጋር ስለነበ

ረች ውዴን እንደ በፊቱ ጠጠርም ሆኑ ቃል አልጣሉባትም ። ዐይናቸው ግን ተከትሏታል ።

ከቤት ሲደርሱ ወ/ሮ ሙሉ እንጀራ ጋግረው ገና እየ ተለቃለቁ ነበርና የእንጀራውና የባህር ዛፉ ሽታ በቤቱ ውስጥ ቱኩስ ጠረን ነበረው ። በትልቁ መወዘቻ ውስጥ በነበረው ሞቅ ያለ ውሀ በሞራ ሳሙና ፊታቸውን እጃቸውንና እግሮቻቸውን ተጣጥበው እንዳበቁ ምሳ ሊያቀርቡ ተጣደፉ ። መኩሪያ ግን ከምሳው በፊት ለብቻቸው ሊያነጋግራቸው እንደሚፈልግ ገልጾላቸው ነጠላቸውን በወጉ ሳይደርቡ ይዟቸው ወደ መንገዱ ወጣ ። የመኪናውን በር ከፍቶ ካስገባቸው በኋላ ስለ ውዴ አባት ማንነት ለመ ንገር ሲል ደረጃ በደረጃ መተረክ ጀመረ ። የቀድሞውን የውብሸትንና የሱን ጓደኝነት ታሪክ ባጭር ባጭሩ ካሳ ወቃቸው በኋላ ወደ መጨረሻው የተጣሉበትንም ምክንያት አስረዳቸው ። ባልተጠበቀ አጋጣሚ ምን ተስኖትና ውብሸት እንዳይላሉ ጐረቤታሞች ሆነው በአንድ የአካባቢ ኮሚቴ ውስጥ እንዲሰሩ በመመረጣቸውና በኋላም በነምንተስኖት ቤት የመጀመሪያው ስብሰባ ሲካሄድ የደ ረሰውን ሁሉ ረጋ ብሎ ገለጸላቸው ። የውብሸት መታመምና ሆስፒታል መተኛት የሕመሙም ጠንቅ እስከ መጨረሻው ግማሽ አካሉን ሽባ እንዳደረገውና አንደበቱም እንደ ታሰረ በጥሞናና በአዘኔታ አስረዳቸው ። ወ/ሮ ሙሉ ፈዘውና ደንግዘው የሚናገሩት መላው ጠፍቷቸው አፋቸውን በነጠላቸው ይዘው "አበስኩ ገበርኩ" ከሚሉ በቀር አንዳችም ቃል ሳይወጣቸው ደንግጠው አዘኑ ።

መኩሪያም ሁኔታውን ከገለጠላቸው በኋላ በዚህ የከፋ ደረጃ ላይ እንዳለ ቢያዩት ለእግዜርም ቢሆን ደስ ሊያሰኘው ይችላል እያለ ስላሳመናቸው ፤ ወ/ሮ ሙሉም በደረሰው ነገር ሁሉ ልባቸው ክፉኛ ስለተነካ ህሊናቸው ውብሸት

እንዳይላሉን በይቅርታ አሰበው ። በዚህም መሠረት በማ
ግስቱ ሰንበት በስምንት ሰዓት ላይ ከውዴ ጋር እንዲ
መጡ በትህትና ለምኗቸው ቃላቸውን ከተቀበለ በኋላ
ምሳ ኤንዲበላ የተማጸኑትን በችኮላው አመካኝቶ ሸኝቷ
ቸው ተለያዩ ።

መኩሪያ በቀጥታ የበረረው ወደ ሲስተር ፋናዬ ቤት
ነበር ። በሁለተኛ ደረጃ በእንጥልጥል የተወውን የሱን
ጉዳይ መልክ ለማስያዝ ምንተስኖትን ማማከሩን ስለወደ
ደው ይህንኑ እያሰላሰለ ደረሰ ፡ ቁልቁል በእንግሊዝ ኤም
ባሲ ትይዩ ወርዶ ዝግ እያለ በማሽከርከር ወደ አካባቢው
ተጠጋ ሰፊው አጥር በርካታ ቤቶችን በውስጡ ከልሎ
ይዟል ። የእያንዳንዱ ቤት ደጃፍ ልዩ ልዩ አበቦችና አትክ
ልቶች ይታዩበታል ። በቤቶቹ መካከል ያለው ሜዳ አረ
ንጓዴ ሆኖ ልምላሜውና ንጽህናው ያምራል ። መኪናውን
ወደ ግቢው ውስጥ እየነዳ ገባ ። ከቤቱ ፊት ለፊት መኪና
ውን አቁሞ ወርዶ እየፈጠነ ሄዶ የነምንተስኖትን ቤት
ቢያንኳኳ ሰው አልነበረምና መልስ አጣ ። ብስጭት ብሎ
ተመልሶ ከመኪናው ውስጥ ገብቶ ለጥቂት ደቂቃ
ተቀመጠ ። የሆስፒታል አዳሩን አሰበው ከዚያ በፊት
ደግሞ ለእናቱ የአዳሩን ሁኔታ ማሳወቅ እንዳለበትም
አልዘነጋም ። ሊወያይበት የመጣውን ጉዳይ በምንተስ
ኖት አለመኖር እንዳለ ጥቅሉን ይዞት መመለሱ ከበ
ደው ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ የግቢውን በር የሚ
ገባ ለመስክ ስራ በየመ/ ቤቱ የሚያገለግለው ቶዮታ ላንድ
ክሩዘር መኪና አየ ። ከሾፌሩ አጠገብ ምንተስኖት መቀ
መጧን መኪናው እየተጠጋ በመጣ ቁጥር ልብ ብሎ አስ
ተዋለ ። የሰውየውን ማንነት ለማወቅ አትኩሮ ቢመለከ
ትም ሊያውቀው አልቻለም ።

ምንተስኖት ከወረደች በኋላ ምስጋናዋን ተቀብሎ
ባለ መኪናው ተመልሶ ከግቢ ወጣ ። ከትከሻው ሰፋ ያለ
ሰማያዊ ኮትና ከወደ ጉልበቷ ሰብሰብ ያለ ጉርድ ቀሚስ
ለብሳለች ። የሰማያዊው ኮትና ጉርድ አላባሽ የሆነው ሸሚ
ዝና ጫማዋ እንዲሁም ቦርሳዋ ነጭ ነበር ። ጸጉር አበጣ
ጠርዋ ፤ አኳኋልዋ ፤ ሌላ ሰው አስመስሏት ነበር ። ተውባ
ታየችው ። በሞቀ ሰላምታዋ ከተቀበለችው በኋላ እንደ
ናፈቀች እህት ጉንጮቹን አገላብጦ ስማ ክንዱን ተደግፋ
ወደ ቤት አመሩ ።

ለብሳው የነበረውን ለውጣ ሞልቀቅ ያለ ረዥም
ቀሚሷን አጥልቃ የቤት ውስጥ ነጠላ ጫማዋን ተጫምታ
ከመጋረጃው ጀርባ ብቅ እስክትል ድረስ መኩሪያ እንደ
ልማዱ መጽሐፍ አንስቶ እየገላለጠ አየ ። ብቅ ስትል
ቀና አለ ። ሁለቱን እጆችዋን ጨብጣ ከጡቷ ስር አስጠ
ግታ እየተፍለቀለቀች “ የምሥራች” አለችው ለመኩሪያ
እሱም በመገረም “ ምስር ብይ ምንቴ ” አላት የሷ ሳቅ
ተጋብቶበት ባላወቀውና ባልሰማው ነገር ከነናው ደስ
ደስ እያለው ።

“ መኩሪያ ሥራ አገኘሁ ዕድሜ ላንተ ” አለችና
እንደገና በተቀመጠበት የደስ ደሱን ሳመችው ። ከፍተኛ
ደስታ ስለ ተሰማው እንደገና ተነስቶ ጨብጧት ስሜቱን
ገለጸላት ። ወዲያውም ቡና እንዲጠጣ ስለ ጋበዘችውና
አዲስ ለተከሰተውም ሆነ ይዞት ለመጣው ሀሳብ መወያያ
ሁኔታ ለመፍጠር ቡና እስከ ሶስተኛ እያፈሉ እየ ጠጡ
መነጋገሩ አማራጭ የሌለው ሆኖ ስለታየው ጥያቄዋን
በእሺታ ተቀበለው ።

ለቡና ሥርዓት የሚገባውን መሰናዶ ሁሉ ካደረገች
በኋላ እቃዎቿን በወግ በወጉ አሰባስባ ከትልቁ ሶፋ ፊት

CamScanner

ለፊት ገለጥ ባለው ሥፍራ ላይ ተቀመጠች ። ምንቴም ልትሰማው የቸኮለችበት ወሬ እንዳለ ሁሉ መኩሪያንም ያጓጓው የምንቴ ሥራ መያዝ እንዴትና በማን በኩል እን ደሆነ ማወቅ ነበር ። ቡናዋን በእርጋታ እያቆላች ወዙ ችፍ ችፍ ማለት ሲጀምርና ሽታው ሲያውድ መንፈሷን ያንጠለጠለውን የውዴንና የውብሸት እንዳይላሉን የት ውውቅ ሁኔታ ለመስማት አስቀድማ ጠየቀችው ። መኩ ሪያ ግን ቋሳና ቅሬታ የቋጠረውን ሁኔታ በቅድሚያ ማው ሳቱ ጨዋታቸውን በመጥፎ ስሜት ሊመርዘው እንደ ሚችል በማሰብ መጀመሪያ ደስታ የፈጠረላቸውን የሥራ መገኘቱን ዜና ዝርዝር ሁኔታ እንድታጫውተው ጠየቃት። ሀሳቡን ተቀብላው ጀበናውን ጥዳ ቡናውን ለመውቀጥ ወጣች ። ትም ትም አድርጋ ፈጥና ከወቀጠችው በኋላ ተመልሳ መጥታ ፈገግታ በፊቷ ላይ እንደደመቀ ለትረ ካዋ ተዘጋጀች ። ለአጀማመሩ እንዲመች በሚል መኩሪያ ካቀረቀረበት መጽሐፍ ላይ ቀና ሳይል ፤

" ማነው እሱ " አላት ። አብሯት የነበረውን ባለ መኪና መጠየቁ ነበር ።

ምንቴም የሆነውን ሁሉ ልታሳውቀው በተዘጋጀ ሁኔ ታዋ አሻግራ እያየችው ጀመረች ።

" ሲስተርና እኔ አብረን መኖር ከጀመርን ዓመታት አለፉ ። በዚህ ጊዜ ውስጥ የአካባቢው ነዋሪ እኔና አንተ እንዳደግንበት መንደርና ባህል በዓላትን አስታኮ ዝክ ርና ድግስን አመካኝቶ መከራም ቢመጣ ተጋግዞ የመገና ኘቱና የመቋቋሙ ሁኔታ እጅግ የሳሳ በመሆኑ ሰው ለሰው ተገናኝቶ አንዱ ሌላውን ማወቅ አይችልም ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን አንድ ቀን ምሽት የደረሰው የመታጠቢያ ውሀ ማሞቂያ መሣሪያ ብልሽት የፈጠረው ጩኸት አደ ናግጦን ባለቤቱም እኛም ዘለን ስንወጣ በዚሁ ሳቢያ ከጐ ረቤታችን ጋር ተዋወቅን ። መደናገጡ በፈጠረው አነስ

ተኛ ችግር የቤቱ ባለቤት በእግሩ ላይ የደም መፍሰስ በመ ድረሱ ሲስተር እርዳታ አደረገችለት ። ይህንን ውለታ በማ ድረግ ከዚያ በኋላ በመንገድ ላይ ሲያገኝን ሰላምታውን አይነፍገንም እኛም አናልፈውም ነበር ። ሥራ አጥ ሆኜ በቤት ውስጥ መዋሌን አስተውሎ ኖሮ በመ/ቤታቸው ክፍት የሥራ ቦታ መኖሩን ሲሰማ እንድወዳደር ነገረኝና ሞከርኩ ። የጽሁፉን ፈተና አልፌ ለቃለ መጠይቅ እንድ ቀርብ የተጠራሁ መሆኑን ነግሮኝ ሄጄ ለጥያቄያቸውም የመሰሉኝን መልሶች ሰጠሁ ። ዛሬ ውጤት ለመስማት ሄጄ ማለፌንና ሥራ በሚቀጥለው ሰኞ እንድጀምር ተነ ግሮኝ መጣሁ ። " አለችው ።

እየተቀላለዱ ከተሳሳቁና በአጋጣሚ ስምረት እየተ ደሰቱ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ወደ መጀመሪያው ጥያቄዋ ተመ ልሳ የውዴን ስሜትና ሁኔታ ለማወቅ ከውብሸት እንዳ ይላሉ ጋር በተደረገው መተዋወቅ ወቅት የሆነውን ሁሉ እንዲነግራት ጉጉት ባደላበት ስሜት ጠየቀችው ። መኩ ሪያም ከመጀመሪያው ጀምሮ የነበረውን የንግግር ልው ውጥ ገለጸላት ። የውብሸትን ዝምድና ከመስማቷ በፊት ጓደኝነታቸውን በተመለከተ የነበራቸውን ጥብቅና ቅርብ ግንኙነት አስታኮ የመጣላታቸውንም ምክንያት በገለጸ ላት ጊዜ የሰጠችውን ትችትና አስተያየት ሳይቀር ነገራት። ይህን ስትሰማ በደልዋንና መከራዋን ልትገነዘብላት በመ ቻልዋ በልጅዋ ብስለትና ወገናዊነት የእርካታ ስሜት ሰረ ጸት ። የአባትነቱን ግንኙነት በሰማች ወቅት የደነገጠ ችውን ድንጋጤ ስትሰማ ግን አዘነች ። ምንቴ ራስዋን በልጅዋ ቦታ በማስቀመጥ ስሜቱንና ድንጋጤውን ለመመ ዘን ሞከረች ። ውብሸትን በተመለከተ ለውዴ ያሳየውን አቅርቦትና ፍቅር ጐላ አድርጐ የሚስቱን ቅራኔ ወደጐን በመተው የአጐቶችዋን አቀባበል በማድነቅ አወራላት ።

ከዚህ በኋላ የሷ ልብ በይቅርታ ጸድቶ እስከ ዕድሜው ማብቂያ ድረስ አካለ ስንኩልና አንደበተ ስንኩል የሆነ ውን በአንድ ወቅት በመተሳሰብና በመዋደድ መልካም ግንኙነት ኖሮት የምታውቀውን ምንም ምድራዊ ኃይል የልጅዋ አባት መሆኑን የማይፍቀውን ሰው ይቅር ብላው እንድትጠይቀው ማነጋገሩና ማሳመኑ በዚያ ሰዓት መሆን እንደሌለበት አመነና ሳያነሳው ቀረ ። ይህንን ጉዳይ ሲስ ተር ፋናዬ ባለችበት መነጋገሩ ከውጤት እንደሚያደር ሰው ስለገመተም ይህን ወደ ጐን ትቶ የራሱን ጉዳይ ሊያ ማክራት ተዘጋጀ ። አቦሉን ቡና ደግሞ እየጠጣ ለብርቱ ምክር መምጣቱን ገለጸላት ። ጉዳዩን ለማወቅ ልቧ ስቅል ብሎ ዓይን ዓይኑን አየችው ።

“ ምንቴ ” አላት ልዩ የወንድምነት ስሜት በሚሰጥ አጠራሩ ፤

“ ምንቴ ፤ ምንም እንኳን የብዙ ዘመን ጥየቄዋ ምኞ ትዋ ሆኖ ነጋ ጠባ ብታሳስበኝም ብትጨቀጭቀኝም አማ ላጅ ብትልክብኝም የኔን ፍላጐት ስላልቀሰቀሰው ጆሮና ትኩረት ሰጥቼው አላውቅም ። እናቴ ትዳር ይዤ ቤት መስርቼ በተለይም የዘርዋን አለመምከን የትውልድ ሀረ ግዋን አለመቋረጥ ማየት ትመኛለች ። ይህን ባውቅም እስከ ዛሬ ምኞትዋን ለማሟላት ብዬ ያደረግሁት ሙከራ የለም ። አሁን ግን የኔም ሀሊና አስፈላጊነቱን እያስገነ ዘበኝ በመምጣቱና በተለይም የሲስተር ተፈጥሮ ፤ ጠባይ አኗኗር ዘይቤ ስለሳበኝ ቀሪ እድሜዬን ከሷ ጋር ባከትመው የሚመቸኝ ሆኖ ስለ ተሰማኝ ባገባት ፤ ብታገባኝ ሀሳብ አለኝ ። ያላትን እቅድ ወይም ታሪክ ከኔ ይልቅ አንቺ ሳታውቂው አትቀሪምና ይህን ሁኔታ ብትገልጪልኝ በም ንስ ሁኔታ ልቀርባት ሀሳቤን ልገልጽላት እንደምችል ብትመክሪኝ እወዳለሁ ” ። አላት ከባድና በርካታ ሆኖ

ያስጨነቀውን ሀሳብ በአጭር ገለጻ አጠናቆ ። ምንቴም የምኞትዋን እምብርት የተመረኮዘ ይህንን ጥያቄ ስትሰማ ደስ ብሏት በሞቀ ፈገግታ በጥሞና ያዳመጠችውን ሀሳብ በመጀመሪያ ደረጃ መደገፏን እንዲሰምርም ጥረት የምታ ደርግበት መሆኑን አስታውቃው ስለ ሲስተር ፋናዬ በኖ ሩበት ጊዜ ውስጥ የምታውቀውን በመመርኮዝ አስተያየ ቷን ሰጠችው ።

ከሲስተር ጋር አብራ በመኖር ከሰማችውና ከታዘ በችው ሁኔታዋ በመነሳት ትዳር መስርቶ ወይም ከሰዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥሮ አሁን ካለችበት የተለየ ኑሮ ለመፍጠር አንዳችም ምኞትና እቅድ እንደ ሌላት ማወ ቋን ብትገልጽለትም ፤ ጥያቄው ሊቀርብላት እንደሚገባና ሀሳብዋን መረዳቱ አማራጭ የሌለው ብቸኛ መነሻ እን ደሆነ አረጋገጠችለት ። ይህንኑም ጥያቄ አመቺ ጊዜና ቦታ በመምረጥ ራሱ መኩሪያ እንዲያቀርብላት ተነጋገሩ ። ምናልባት የማትቀበለው ቢሆን ሀሳብዋን ለማስለወጥ በጓደኝነቷና በቀረቤታዋ ሳቢያ ስሜቷን ለማለዘብ ውሳ ኔዋን ለማላላት ጥረት እንደምታደርግ ካረጋገጠችለት በኋላ ውይይታቸውን ቋጥረው ፤ መኩሪያም እናቱን አይቶ ወደ ሆስፒታል አዳሩ ሊሻገር ተሰናብቷት ወጣ ። ከበረን ዳው አልፋ ጥቂት ርቀት ተከትላው ከሸኘችው በኋላ ከመኪናው ገብቶ ከዐይኗ እስኪሰወር ድረስ ቆማ ተመለ ከተችው ። በተሟላ አካላዊና መንፈሳዊ አቋም ሰብአዊ ሕልውናዋን ተጐናጽፋ በረሳት ኅብረተሰብ መካከል እንደገና እንድትራመድ ዳግም የሕይወት ምርኩዝ ያስ መረኮዛትን መኩሪያን በቆመችበት ከልቧ አመሰገነችው። በአለኝታነቱ ኮራችበት ። ለሱ ሕይወት መድመቅ የሷን ሕይወት ማንደድ ቢያስፈልግ እንኳን ላትቆጠብ ማለች ።

CamScanner